## ቅዳሴ ፡ አትናቴዎስ ።

፩ ፤ አኰቴተ ፡ ቍርባን ፡ ዘቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

፪ ፤ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

ይ ፡ ካ ፡ አእኵትዎ ፡ ለአምላክነ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ርቱዕ ፡ ይደሉ ።

## የአትናቴዎስ ፡ ቅዳሴ ።

፩ ፤ የእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ የተናገረው ፡ የቍርባን ፡ ምስጋና ። ጸሎቱና ፡ በረከቱ ፡ ከሁላችን ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑር ።

፪ ፤ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሁላችሁ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከመንፈስህ ፡ ጋራ ።

ይ ፡ ካ ፡ አምላካችንን ፡ አመስግኑት ።

ይ ፡ ሕ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይገባል ።

ይ ፡ ካ ፡ አልዕሉ ፡ አልባቢክሙ ።
ይ ፡ ሕ ፡ ብነ ፡ ኀበ ፡ እግዚብሔር ፡ አምላክነ ።

፫ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ዮም ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ እለ ፡ ተጋባእክሙ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጽምዑ ፡ ቅዳሴሃ ፡ ለሰንበተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ።
፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ አሰምዕ ፡ ለክሙ ፡ ሰማያተ ፡ አሰምዕ ፡ ለክሙ ፡ ምድረ ፡ ከመ ፡ ትቁሙ ፡ በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ፡ ዘእንበለ ፡ ተሀውኮ ።

፭ ፡ ወኢመኑሂ ፡ ኢየሀሉ ፡ ዝየ ፡ በመዓት ፡ ምስለ ፡ እኁሁ ፡ ከመ ፡ ቃየል ፡ እንዘ ፡ መስተበቅል ፡ ውእቱ ።

፮ ፡ ወኢመኑሂ ፡ ኢየሀሉ ፡ ዝየ ፡ በተቃርኖ ፡ ምስለ ፡ ቢጹ ፡ ከመ ፡ ዳታን ፡ ወአቤሮን ፡ እለ ፡ ተቃረንዎ ፡ ለሙሴ ።
፯ ፡ ወኢመኑሂ ፡ ኢየሀሉ ፡ ዝየ ፡ በተንሕልዎ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፡ ከመ ፡ ከይሲ ፡ ዘፈየታ ፡ ለሔዋን ።

፰ ፡ አ ፡ ካህናት ፡ አንትሙ ፡ ውእቱ ፡ አዕይንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሩሃት ። ተናጸሩ ፡ በበይናቲክሙ ፡ ፩ዱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፡ ሕቱ ፡ እምውስተ ፡ ሕዝብክሙ ፡ በአበይና ፡ ኢይቁም ፡ ወኢይኅበር ፡ ምስሌክሙ ፡ በጸልዮ ፡ ኢዘማዊ ፡ ወኢቀታሊ ፡ ወዘያጣዑ ፡ ኢሰራቂ ፡ ወኢሐማዊ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ፭ቱ ፡ አክላብ ፡ እለ ፡ በአፍአ ፡ ይትኴነኑ ።

፱ ፡ ገሥጽዎ ፡ ለኃጥእ ፡ ከመ ፡ እኁክሙ ፡ ዝልፍዎ ፡ በግሀደት ፡ ለእመ ፡ ቦቱ ፡ አበሳ ፡ ዘለሞት ።
፲ ፡ መዐድዎ ፡ ለዘኤገየ ፡ ከመ ፡ ይኅድግ ፡ ኪያሃ ፡ ፍኖተ ፡ ወይትጋነይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይሥረይ ፡ ሎቱ ።
፲፩ ፡ አ ፡ ዲያቆናት ፡ ማኅቶተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወላእካኒሃ ፡ ምልኑ ፡ እምውስቴታ ፡ ኢየሀሉ ፡ ተዘኣላ ፡ ምስለ ፡ በግዕ ፡ አንቁ ፡ ምስለ ፡ ርግብ ፡ ክርዳድ ፡ ምስለ ፡ ሥርናይ ።

ይ ፡ ካ ፡ ልቡናችሁን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጉ ።
ይ ፡ ሕ ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አለን ።
፫ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ዛሬ ፡ በዚህች ፡ ቀን ፡ በዚህች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ውስጥ፡የተሰበሰባችሁ ፡ ምእመናን ፡ ክብርት ፡ የምትሆን ፡ የክርስቲያንን ፡ ሰንበት ፡ ቅዳሴ ፡ ስሙ ።
፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ሰማያትን ፡ አዳኝባችኋለሁ ። ምድርንም ፡ አዳኝባችኋለሁ ። ያለ ፡ መታወክ ፡ በፍርሃትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ ትቆሙ ፡ ዘንድ ።
፭ ፡ እንደ ፡ ቃየል ፡ በቀለኛ ፡ ሆኖ ፡ ከወንድሙ ፡ ጋራ ፡ ማንም ፡ ከዚህ ፡ በመዓት ፡ አይኑር ።

፮ ፡ ሙሴን ፡ እንደ ፡ ተጣሉት ፡ እንደ ፡ ዳታንና ፡ እንደ ፡ አቤሮን ፡ ከባልንጀራው ፡ ጋራ ፡ ማንም ፡ በመጣላት ፡ ከዚህ ፡ አይኑር ።
፯ ፡ ሔዋንን ፡ እንዳሳታት ፡ (እንደ ፡ ቀማት ፡) እባብ ፡ ( ወንድሙ ፡ ጋራ ፡ በመሸነጋገል ፡ ማንም ፡ ከዚህ ፡ አይኑር ።

፰ ፡ ካህናት ፡ ሆይ ፡ ብሩሃን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዓይኖች ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ። እርስበርሳችሁ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ ተመልካከቱ ፡ ከወገናችሁ ፡ ውስጥ ፡ በፈሊጥ ፡ መርምሩ ፡ በመጸለይ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ እንዳይቆምና ፡ እንዳይተባበር ፡ ሴሰኛም ፡ ቢሆን ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይም ፡ ቢሆን ፡ ጣዖት ፡ የሚያመልክም ፡ቢሆን ፡ ሌባም ፡ ቢሆን ፡ ሐሰተኛም ቢሆን ፡ እሊኸውም ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማይ በአፍአ ፡ የሚፈረድባቸው ፡ አምስት ፡ ውሾች ፡ ናቸው ።
፱ ፡ ኃጢአተኛውን ፡ እንደ ፡ ወንድማችሁ ፡ ገሥጹት ፡ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ በደል ፡ ቢኖርበት ፡ በግልጽ ፡ ዝለፉት ።
፲ ፡ የበደለውን ፡ ምከሩት ፡ ያችን ፡ መንገድ ፡ ይተው ፡ ዘንድ ፡ ይቅር ፡ ሊልለት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ።
፲፩ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መብራት ፡ አገልጋዮቿዋም ፡ የምትሆኑ ፡ ዲያቆናት ፡ ሆይ ፡ ተኩላ ፡ ከበግ ፡ ጋራ ፡ ጭላት ፡ ከርግብ ፡ ጋራ ፡ ክርዳድ ፡ ከስንዴ ፡ ጋራ ፡ እንዳይኖር ፡ ከውስጥዋ ፡ ንቀሉ ።

፲፪ ፤ አንትሙሰ ፡ ሕቱ ፡ እንተ ፡ አፍአ ፡ ወአኮ ፡ እንተ ፡ ውስጥ ፡ ወእንቲ ፡ ውስጥሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአምር ። ወይፈትን ፡ በማኅቶተ ፡ ዚአሁ ።

፲፫ ፡ ይ ፡ ዲ ፤ እለ ፡ ትነብሩ ፡ ተንሥኡ ።

፲፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ይትረኃዋ ፡ አእዛነ ፡ ልብ ፡ ዘውስጥ ፡ ወአኮ ፡ አእዛን ፡ እለ ፡ ትኩላት ፡ በአፍአ ። ይትከሠታ ፡ አዕይንተ ፡ ልብ ፡ ዘውስጥ ፡ ወአኮ ፡ አዕይንት ፡ እለ ፡ ብሩሃት ፡ በአፍአ ።

፲፭ ፤ ወኢይኩን ፡ ኅሊናነ ፡ ከመ ፡ መዋግደ ፡ ባሕር ፡ ምዕረ ፡ ዘየዐርግ ፡ ላዕለ ፡ ወምዕረ ፡ ዘይወርድ ፡ ታሕተ ፡ አላ ፡ ይኩን ፡ ከመ ፡ ዐምደ ፡ እሳት ፡ እምድር ፡ ዘይበጽሕ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ።

፲፮ ፤ ወይኩን ፡ ልብነ ፡ ስፉሐ ፡ በፈሪሃ ፡ ዚአሁ ፡ ከመ ፡ መንጦላዕተ ፡ ወርቅ ፡ ዘጽፉቅ ፡ እንመቲ ።

፲፯ ፤ ናንሥእ ፡ እደዊነ ፡ ኀቤሁ ፡ ወንስፉሕ ፡ የማነ ፡ ወጸጋመ ፡ ከመ ፡ ሰይፈ ፡ እሳት ፡ ዘውእቱ ፡ ያፈርሆ ፡ ለሰይጣን ፡ በከመ ፡ ተብህለ ።

፲፰ ፡ ወይኩን ፡ እገሪነ ፡ ትኩለ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ቅትራተ ፡ ሐዊን ፡ ዘኢያንቀለቅል ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ በዘከመዝ ፡ ኅሀሉ ፡ እግዚአብሔር ይሬኢ ።

፲፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ውስተ ፡ ጽባሕ ፡ ነጽሩ ።

፳ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ሰብእሰ ፡ እንዘ ፡ ክቡር ፡ ውእቱ ፡ ኢያእመረ ። ወኮነ ፡ ከመ ፡ እንስሳ ፡ ዘአልቦ ፡ ልብ ፡ ወተመሰሎሙ ።

፳፩ ፤ ሰብእሰ ፡ እንዘ ፡ ንጉሥ ፡ ውእቱ ፡ ኢያእመረ ። አኅሠረ ፡ ርእሶ ፡ በፈቃዱ ፡ ወኮነ ፡ ገብረ ፡ ወመለክዎ ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ አጋእዝተ ።

፳፪ ፤ ሰብእሰ ፡ እንዘ ፡ ባዕል ፡ ውእቱ ፡ ኢያእመረ ። አንደየ ፡ ርእሶ ፡ በሥምረቱ ፡ አርኀበ ፡ ከርሦ ፡ ወአጽምዐ ፡ ነፍሶ ።

፳፫ ፤ አ ፡ እግዚኦ ፡ አንተሰ ፡ ሚመጠን ፡ ዘገበርከ ፡ ሎቱ ፡ ለሰብእ ። ሰፋሕከ ፡ ሰማየ ፡ ከመ ፡ ቀመር ፡ ለአንክሮቱ ፡ ወአርነብከ ፡ ምድረ ፡ ለኪደተ ፡ እግሩ ።

፲፪ ፡ እናንተስ ፡ የውስጡን ፡ ያይደለ ፡ የአፍአውን ፡ መርምሩ ፡ የውስጡን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ። በርሱ ፡ መብራትም ፡ ይመረምራል ።

፲፫ ፤ ዲ ፡ ዲ ፡ የተቀመጣችሁ ፡ ተነሡ ።

፲፬ ፤ ይ ፡ ካ ፡ በአፍአ ፡ የተተከሉ ፡ ጆሮዎች ፡ ያይደሉ ፡ የውስጣዊ ፡ ልብ ፡ ጆሮዎች ፡ ይከፈቱ ። በአፍአ ፡ የሚያበሩ ፡ ዓይኖች ፡ ያይደሉ ፡ የውስጣዊ ፡ ልብ ፡ ዓይኖች ይገለጡ ።

፲፭ ፡ አሳባችን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እንደሚወጣ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደታች ፡ እንደሚወርድ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አዟሪ ፡ አይሁን ። ከምድር ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ እንደሚደርስ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ምሰሶ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ።

፲፮ ፡ ሥራው ፡ ጽፍቅ ፡ እንደሆነ ፡ እንደወርቅ ፡ መጋረጃ ፡ ልቡናችን ፡ እርሱን ፡ በመፍራት ፡ የተዘጋጀ ፡ ይሁን ።

፲፯ ፡ እጆችንን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ እናንሣ ። እንደ ፡ እሳት ፡ ሰይፍ ፡ ወደ ፡ ቀኝና ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ እንዘርጋ ። ይኸውም ፡ እንደተነገረ ፡ ሰይጣንን ፡ የሚያስፈራው ፡ ነው ።

፲፰ ፡ እግራችን ፡ ሁል፡ጊዜ፡ በመዓልትም በሌሊትም ፡ እንደማይናወጥ ፡ እንደብረት ፡ ችንካር ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር፡የተተከለ ፡ ይሁን ። ሁልጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ አነዋወር፡ እንኑር ፡ እግዚአብሔር፡ ሲያይ ።

፲፱ ፤ ዲ ፡ ዲ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ተመልከቱ ።

፳ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ክቡር ፡ ሲሆን ፡ አላወቀም ። ልብ ፡ እንደሌለው፡ እንደ፡እንስሳም ፡ ሆነ ፡ መሰላቸውም ።

፳፩ ፡ ሰውስ ፡ ንጉሥ ፡ ሲሆን ፡ አላወቀም በፈቃዱ ፡ ራሱን ፡ አዋረደ ፤ ባሪያም ፡ ሆነ ፡ ጌቶች ፡ ያልሆኑትም ፡ ገዙት ።

፳፪ ፡ ሰውስ ፡ ባለጸጋ ፡ ሲሆን ፡ አላወቀም ፡ በፈቃዱ ፡ ራሱን ፡ ነዳይ ፡ አደረገ ፡ ሆዱን ፡ አስራበ ፡ ነፍሱንም ፡ አስጠማ ።

፳፫ ፡ አቤቱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ያደረግህለት ፡ ቸርነት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ። ሊያደንቅበት ፡ ሰማይን ፡ እንደ ፡ ድንኳን ፡ ዘረጋህ ፡ ምድሩንም ፡ ለእግሩ ፡ መመላለሻ ፡ አሰፋህ ።

፳፬ ፡ ተዐቍር ፡ ማየ ፡ በከርሠ ፡ ደመና ፡
ለሲሳዩ ። አብራህከ ፡ ፀሓየ ፡ ከመ ፡ ይትፌ
ሣሕ መዓልተ ። ወአሠነይከ ፡ ወርኀ ፡ ከመ
ኢይድፍኖ ፡ ጽልመተ ፡ ሌሊት ፡ ወአፅደ
ልከ ፡ ብርሃነ ፡ ከዋክብት ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡
ግብረ ፡ አጻብዒከ ፡ ወወሀብኮ ፡ ዕለታተ ፡
ወዓመታተ ፡ አዝማነ ፡ ወመዋዕለ ፡ ከመ ፡
ይትጋነይ ፡ ለከ ።

፳፭ ፡ ኦ ፡ ለይብቡት ፡ ልቡ ፡ ለሰብእ ፡ አር
አይኮ ፡ ሞተ ፡ ወሕይወተ ። አፍቀረ ፡ ሞተ ፡
ወመነነ ፡ ሕይወተ ። አኮ ፡ ሞት ፡ ዘሥጋ ፡
ከመ ፡ ንዋም ፡ ለእንተ ፡ ምዕር ፡ ለሰዓት ፡
እስከ ፡ ጊዜሁ ፡ ለጻድቃን ፡ ወለኃጥአን ፡
ዘተሠርዐ ፡ አላ ፡ ሞት ፡ ዘለዓለም ፡ ወለዓ
ለመ ፡ ዓለም ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ ፡ ወኢተ
ፍጻሜት ።

፳፮ ፡ ሰብእሰ ፡ እንዘ ፡ ልቡስ ፡ ውእቱ ፡
ልብሰ ፡ ብርሃን ፡ አዕረቀ ፡ ሥጋሁ ፡ ወተ
ከድነ ፡ አዕጻለ ፡ ዘማዕሰ ።

፳፯ ፡ ሰብእሰ ፡ እንዘ ፡ መላኪ ፡ ውእቱ ፡
እምታሕተ ፡ እግዚእ ፡ ሠረቀ ፡ ወበልዐ ፡
እምዕፅ ፡ ዘኢተአዘዞ ፡ ሎቱ ።

፳፰ ፡ ኦ ፡ አዳም ፡ ምንተኑ ፡ ረሰይናከ ፡
ዘአምጻእከ ፡ ፍትሐ ፡ ሞት ፡ ላዕሌነ ። ኦ ፡
አዳም ፡ ምንተኑ ፡ ረሰይናከ ፡ ዘኢኀደገነ ፡
ንትፌጋዕ ፡ በእንተ ፡ ፍግዕ ፡ በአብያተ ፡
እግዚእ ።

፳፱ ፡ ኦ ፡ ሔዋን ፡ ምንተኑ ፡ ረሰይናኪ ፡
ናሁ ፡ ጸልመ ፡ ሥጋነ ፡ በብዝኀ ፡ ኃጣውእ ።
ዘእምነበርነ ፡ በአርአያ ፡ ሰማያውያን ።

፴ ፡ ኦ ፡ ሔዋን ፡ ምንተኑ ፡ ረሰይናኪ ፡
ናሁ ፡ ይበክያ ፡ ኵሎን ፡ አዋልድኪ ፡ ሶበ ፡
ይወልዳ ፡ በፃዕር ፡ ወሕማም ፡ ወይደምፃ ፡
በከመ ፡ አድመውኪዮ ፡ አንቲ ፡ ለእንትኩ ፡
ዕፅ ፡ ዘውስተ ፡ ገነት ።

፴፩ ፡ ኦ ፡ አዳም ፡ ወሔዋን ፡ እስመ ፡ አኮ ፡
ዘይትከሀል ፡ ኪያክሙ ፡ ንጽዐል ፡ በከመ ፡
ለልሳን ፡ ዘኢይትከሀል ፡ ይጽዐልዎ ፡ እንዘ ፡
ይትናገሩ ፡ ቦቱ ። ወከማሁ ፡ አንትሙ ፡
ንህነ ፡ ወንህነ ፡ አንትሙ ።

፳፬ ፡ ውኃን ፡ ለምግቡ ፡ በከርሠ ፡ ደመና፡
ትቋጥራለህ ፡ በመዓልት ፡ ደስ ፡ ይለው ፡
ዘንድ ፡ ፀሐይን ፡ አበራህ ፡ የሌሊት ፡ ጨለ
ማም ፡ እንዳይሸፍነው ፡ ጨረቃን ፡ አሳ
መርሀለት ። የጣቶችህንም ፡ ሥራ ፡ ያውቅ ፡
ዘንድ ፡ የከዋክብትን፡ብርሃን ፡ አበራህለት ።
ዕለታትንና ፡ ዓመታትን ፡ ዘመናትንና ፡ ወራ
ትን ፡ ሰጠኸው ፡ ይገዛልህ ፡ ዘንድ ።

፳፭ ፡ ልቡ ፡ ለደረቀች ፡ ለሰው ፡ ወዮለት ፡
ሞትንና ፡ ሕይወትን ፡ አሳየኸው ፡ ሕይወ
ትን ፡ ንቆ ፡ ሞትን ፡ ወደደ ። እስከ ፡ ጊዜው ፡
ለጻድቃንና ፡ ለኃጥኣን ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡
ሳንዲት ፡ ጊዜ ፡ ለሰዓት ፡ እንደሚሆን ፡ እን
ቅልፍ ፡ የሥጋ ፡ ሞት ፡ አይደለም ፡ ቍጥር ፡
ፍጻሜ ፡ የሌለው ፡ ለዓለም ፡ ለዘለዓለም ፡
የሚሆን ፡ ሞት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፳፮ ፡ ሰውስ ፡ የብርሃን ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡
ሲሆን ፡ ሰውነቱን ፡ አራቆተ ። የዳባ ፡ ልብ
ስን ፡ ለበሰ ።

፳፯ ፡ ሰውስ ፡ ከጌታ ፡ በታች ፡ ገዢ ፡
ሲሆን ፡ ካልታዘዘለት ፡ ዕፅ ፡ ሠርቆ ፡ በላ ።

፳፰ ፡ አዳም ፡ ሆይ ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡
ያመጣህብን ፡ ምን ፡ አደረግንህ ። አዳም ፡
ሆይ ፡ ደስታ ፡ ባለበት ፡ በገነት ፡ በጌታ ፡
ማደሪያ ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡ ያልተው
ኸን ፡ ምን ፡ አደረግንህ ።

፳፱ ፡ ሔዋን ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ አደረግንሽ ፡
እነሆ ፡ በኃጢአት ፡ ብዛት ፡ ሥጋችን ፡
ጠቆረ ፡ በሰማያውያን ፡ አምሳል ፡ በኖርን ፡
ነበረ ።

፴ ፡ ሔዋን ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ አደረግንሽ ።
እነሆ ፡ ልጆችሽ ፡ በጭንቅና ፡ በሕማም ፡
በወለዱ ፡ ጊዜ ፡ ያለቅሳሉ ፡ አንቺ ፡ ያችን ፡
በገነት ፡ ያለችውን ፡ ዕንጨት ፡ እንዳደማ
ሻት ፡ ይደማሉ ።

፴፩ ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ሆይ ፡ እናንተን
እንነቅፍ ፡ ዘንድ ፡ የሚቻል ፡ አይደለም ፡
እኮ ፡ አንደበትን ፡ እየተናገሩበት ፡ ሊሰድ
ቡትና ፡ ሊነቅፉት ፡ እንዳይቻል ፡ እን ደዚ
ህም ፡ እናንተ ፡ እኛን ፡ ናችሁ ፡ እኛም ፡
እናንተን ፡ ነን ።

፴፪ ፡ አ ፡ አዳም ፡ ወሔዋን ፡ አንትሙሰ ፡ ነሳሕያን ፡ በተግሣጸ ፡ እግዚእ ፡ መሐሪ ። አ ፡ አዳም ፡ ወሔዋን ፡ አንትሙሰ ፡ በአማን ድኅናን ፡ወቦእክሙ ፡ ኀበ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ርስትክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ክልኤት ፡ በደመ ፡ ዚአሁ ፡ ለዘተበ.ዘወክሙ ። ወኵሎሙ ፡ ዐላውያን ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ በዘተበ.ዘወክሙ ፡ ኢኮኑ ፡ ደቂቀክሙ ፡ አላ ፡ አርአያክሙ ፡ ወአምሳሊክሙ ።

፴፫ ፡ ወንሕነሰ ፡ እለ ፡ አመነ ፡ በዋሕድ ፡ ወልድክሙ ፡ በአማን ፡ ንሀነ ፡ አርአያክሙ ፡ ወአምሳሊክሙ ፡ እለ ፡ ወፃእነ ፡ እምሐቌክሙ ።

፴፬ ፡ ናሁ ፡ ለደቂቅክሙ ፡ በልዐተነ ፡ ኃጢአት ፡ ከመ ፡ ዘእሳት ፡ ወአውዐየተነ ፡ ፍትወት ፡ አኮ ፡ ፍትወት ፡ ዘነፍስ፡ አላ፡ፍትወት ፡ ዘሥጋ ። ዘውእቱ ፡ ማኅጎሊሃ ፡ ለነፍስ ።

፴፭ ፡ እምይእዜሰ ፡ ንበል ፡ ሰላም ፡ ለኪ ፡ አ ፡ ገነተ ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘኢይትከሀል ፡ ንባእ ፡ ኀቤኪ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ በድርዐ ፡ እንግድዓ ።

፴፮ ፡ ሰላም ፡ ለኪ ፡ አ ፡ ሔዶም ፡ ገነት ፡ እንተ ፡ አበውነ ፡ አዳም ፡ ዘኢይትከሀል ፡ናን ፈርዕዐ ፡ በውስቴትኪ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ እመ ፡ ኢየሃመውነ ፡ ሥጋነ ፡ በገዘየ ።

፴፯ ፡ ሰላም ፡ ለኪ ፡ አ ፡ ምድረ ፡ ገነት ፡ ዘኢይትከሀል ፡ ናሶሱ ፡ በውስቴትኪ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ እመ ፡ ኢከላእነ ፡ እገሪነ ፡ እምአንሶስዎ ፡ በከንቱ ።

፴፰ ፡ ወካበ ፡ ንበል ፡ አ ፡ ሱራፊ ፡ ዐቃቢሃ ፡ ለገነት ፡ ዘበሰይፈ ፡ እሳት ፡ ኅድገነ ፡ ንባእ ፡ ወንርአያ ፡ ለአብያተ ፡ እግዚእ ፡ ወአኮ ፡ ዘንነብር ፡ ውስቴታ ።

፴፱ ፡ አ ፡ ሱራፌ ፡ ኅድገነ ፡ ንባእ ፡ ንርአያ ፡ ለማኅደረ ፡ ሕይወት ፡ ወአኮ ፡ ዘንትኀባእ ፡ሀየ ።

፵ ፡ አ ፡ ሱራፌ ፡ ኅድገነ ፡ ንባእ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ ወናጼኑ ፡ አፈዋቲሃ ፡ ወይሠወጥ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ መዓዛ ፡ ዚአሃ ።

፴፪ ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ሆይ ፡ እናንተስ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ በሆነ ፡ ጌታ ፡ ተግሣጽ ፡ ንስሓ ገብታችኋል ።

አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ሆይ ፡ እናንተስ ፡ በውነት ፡ ድናችኋል ፡ በተበጀችሁ ፡ በጌታ ፡ ደም ፡ ያለ ፡ መከልከል ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ርስታችሁ ፡ ገብታችኋል ። በተበጀችሁ ፡ በጌታ የማያምኑ ፡ ዐላውያን ፡ ሁሉ ፡ ልጆቻችሁ ፡ አይደሉም ። አርአያችሁ ፡ ምሳሌያችሁ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ።

፴፫ ፡ በአንድ ፡ ልጃችሁ ፡ ያመን ፡ እኛ ፡ ግን ፡ በዕውነት ፡ ከወገባችሁ ፡ የወጣን ፡ አርአያችሁ ፡ ምሳሌዎቻችሁ ፡ ነን ።

፴፬ ፡ እነሆ ፡ እኛን ፡ ልጆቻችሁን ፡ ኃጢአት ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ በላችን ። ፍትወትም ፡ አቃጠለችን ። የነፍስ ፡ ፍትወት ፡ አይደለም ፡ የሥጋ ፡ ፍትወት ፡ ነው ፡ እንጂ ። ይኸውም ፡ ነፍስን ፡ የሚያጠፋት ፡ ነው ።

፴፭ ፡ እንግዲህስ ፡ የደስታ ፡ ገነት ፡ ሆይ ፡ ሰላም ፡ ላንቺ ፡ ይሁን ፡ እንበል ። በመጨከን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወዳንቺ ፡ እንገባ ፡ ዘንድ የማይቻለን ።

፴፮ ፡ የአባታችን ፡ የአዳም ፡ ሔዶም ፡ ገነት ፡ ሆይ ፡ ሰላም ፡ ላንቺ ፡ ይሁን ፡ በውስጥሽ ፡ ደስ ፡ ሊለን ፡ የማይቻል ፡ በዚህ ፡ ሥጋችንን ፡ ካላደከምን ፡ በቀር ።

፴፯ ፡ የገነት ፡ ምድር ፡ ሆይ ፡ ሰላም ፡ ላንቺ ፡ ይሁን ፡ በውስጥሽ ፡ ልንመላለስ ፡ የማይቻል ፡ እግሮቻችንን ፡ በከንቱ ፡ ከማመላለስ ፡ ካልከለከልን ፡ በቀር ።

፴፰ ፡ ዳግመኛም ፡ በእሳት ፡ ሰይፍ ፡ ገነትን ፡ የምትጠብቅ ፡ ሱራፊ ፡ ሆይ ፡ የጌታን ፡ ማደሪያ ፡ ገብተን ፡ እናያት ፡ ዘንድ ፡ ተወን ፡ እንበል ። በውስጧም ፡ የምንኖር ፡ አይደለም ።

፴፱ ፡ ሱራፊ ፡ ሆይ ፡ የሕይወት ፡ ማደሪያን ፡ (ገነትን ፡) ገብተን ፡ እናያት ፡ ዘንድ ፡ ተወን ። በዚያ ፡ የምንሸሸግ ፡ አይደለም ።

፵ ፡ ሱራፌ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ገብተን ፡ ሽቱዋን ፡ እናሽት ፡ ዘንድ ፡ ተወን ። መዓዛዋም ፡ በልቡናችን ፡ ይጨመር ፡ ዘንድ ።

፶፩ ፤ አ ፡ ሡራሬ ፡ ኅድገነ ፡ ንባእ ፡ ውስተ
**ዘቀዳሚ** ፡ ርስተ ፡ አቡነ ፡ ከመ ፡ ንትፈሣሕ ፡
**በዕፀዊሃ** ፡ ወአኮ ፡ ዘንቀጥፍ ፡ **እምፍሬሃ** ፡
**በአእዳው** ፡ ከመ ፡ ዘትካት ።

፶፪ ፡ አ ፡ ሡራሬ ፡ ኅድገነ ፡ ንባእ ፡ ንርአ
የውሙ ፡ ለወሐይዝተ ፡ ብርሃን ፡ እለ ፡ ይሠቅ
ይዋ ፡ ለገነተ ፡ ግዮን ፡ ወኤፌሶን ፡ ጤግሮስ ፡
ወኤፍራጥስ ።

፶፫ ፡ ቦ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምሥራቅ ፡ ወየሐ
ውር ፡ ለምዕራብ ፡ ከመ ፡ ይሥቂ ፡ ዘህየ ።

፶፬ ፡ ቦ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምዕራብ፡ወየሐውር
ለምሥራቅ ፡ ከመ ፡ ይሥቂ ፡ ዘህየ ።

፶፭ ፡ ቦ ፡ ዘይነቅዕ ፡ እምደቡብ ፡ ወይሠ
ወጥ ፡ ለሰሜን ፡ ከመ ፡ ይሥቂ ፡ ዘህየ ።

፶፮ ፤ ወቦ ፡ ዘይፈለፍል ፡ እምሰሜን ፡ ወይ
ሠወጥ ፡ ለደቡብ ፡ ከመ ፡ ይሥቂ ፡ ዘህየ ።
በከመ ፡ ተብህለ ፡ መንክር ፡ ተላህያ ፡ ለባ
ሕር ፡ ወኩማሁ ፡ መንክር ፡ ውእቱ ፡ ተላህዮ
ቶን ፡ ለአፍላግ ፡ ዘእንበለ ፡ ድምፅ ። ምንተ ፡
ንብል ፡ ወንዛዋዕ ፡ ከመ ፡ መሰንቆ ፡ ዘአልቦ፡
ነፍስ ።

፶፯ ፡ ወንሕነሰ ፡ እለ ፡ ቅቡዓን ፡ በጸጋ ፡
እግዚአብሔር ፡ በአማን ፡ ክርስቲያን ፡ ክር
ስቶሳውያን ፡ ወመሢሓውያን ፡ ንጽሐቅ ፡
ወንጒጓዕ ፡ ንቅናዕ ፡ ወንቅረብ ፡ ከመ ፡
ንባእ ፡ እምክብር ፡ ውስተ ፡ ክብር ።
መቅድመ ፡ ናግርር ፡ ለሥጋነ ፡ ወናስተጋ
ብእ ፡ ሕሊናነ ፡ እምዝርወት ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡
ከመ ፡ ተሰጢዎ ፡ ይትወከፍ ፡ ጸሎተነ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

፶፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንነጽር ።
፶፱ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አኮ ፡ ብነ ፡ ዝየ ፡ ሀገር ፡ አጽ
ናፍ ፡ ወጕጻጉጽ ፡ ወመብዕስ ፡ ዘኢኮነ ፡
ርቱዐ ። አላ ፡ ዘበላዕሉ ፡ ኀበ ፡ ዘቀደሙ ፡
በጺሐ ፡ ነቢያት ፡ ወሐዋርያት ።

፶፩ ፤ ሡራሬ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ አባ
ታችን ፡ ርስት ፡ እንገባ ፡ ዘንድ ፡ ተወን ።
በዕንጨቶቿ ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡
ቀድሞ ፡ ከፍሬዋ ፡ በእጃችን ፡ የምንቆርጥ ፡
አይደለም ።

፶፪ ፤ ሡራሬ ፡ ሆይ ፡ ገነትን ፡ የሚያጠ
ጡት ፡ የብርሃንን ፡ ወንዞች ፡ ግዮንንና ፡
ኤፌሶንን ፤ ጤግሮስንንና ፡ ኤፍራጥስን ፡
ገብተን ፡ እናያቸው ፡ ዘንድ ፡ ተወን ።

፶፫ ፤ ከምሥራቅ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ምዕ
ራብ ፡ የሚሄድ ፡ አለ ፤ በዚያ ፡ ያለውን ፡
ያጠጣ ፡ ዘንድ ።

፶፬ ፤ ከምዕራብ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ
የሚሄድ ፡ አለ ፡ በዚያ ፡ ያለውን ፡ ያጠጣ ፡
ዘንድ ።

፶፭ ፤ ከደቡብ ፡ ነቅቶ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡
የሚጨመር ፡ አለ ፡ በዚያ ፡ ያለውን ፡ ያጠጣ
ዘንድ ።

፶፮ ፤ ከሰሜን ፡ መንጭቶ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡
የሚጨመር ፡ (የሚሄድ ፡) አለ ፤ በዚያ ፡ ያለ
ውን ፡ ያጠጣ ፡ ዘንድ ።
የባሕር ፡ መመላለሷ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡
እንደ ፡ ተባለ ፤ እንዲሁም ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡
የአፍላግ ፡ መመላለሳቸው ፡ ድንቅ ፡ ነው ።
ምን ፡ እንላለን ፡ ነፍስ ፡ እንደሌለውም ፡
እንደ ፡ መሰንቆ ፡ እንጫወታለን ።

፶፯ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ የተቀባን ፡
በእውነት ፡ ክርስቲያን ፡ የክርስቶስ ፡ ወገ
ኖች ፡ መሢሓውያን ፡ እኛ ፡ ግን ፡ እንትጋ ፡
እንቸኵልም ። እንቅና ፡ ከክብር ፡ ወደ ፡
ክብር ፡ እንገባም ፡ ዘንድ ፡ እንቅረብ ።
አስቀድሞ ፡ ሥጋችንን ፡ እናስገዛው ፡ ሁል
ጊዜ ፡ አሳባችንን ፡ ከመባከን ፡ እንሰብስብ ፡
አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዶ ፡ ልመ
ናችንን ፡ ይቀበልልን ፡ ዘንድ ።

፶፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ እናስተውል ።
፶፱ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ገደል ፡ ጕጻጉጽ ፡ ቀና ፡
ያይደለ ፡ ጠማማ ፡ የሆነ ፡ አገር ፡ ከዚህ ፡
ያለን ፡ አይደለም ። ነቢያትና ፡ ሐዋርያት ፡
አስቀድመው ፡ የደረሱበት ፡በልዕልና ፡ ያለ ፡
ነው ፡ እንጂ ።

፶ ፤ አኮ ፡ ብነ ፡ ዝየ ፡ አብያት ፡ ዘሕኑፅ ፡ በኖፃ ፡ ዘይነፍሕዎ ፡ ነፋሳት ፡ ወይገፍእዎ ፡ ወሐይዝት ። አላ ፡ ዘበላዕሉ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አግዓዚት ፡ ኀበ ፡ ቀደሙ ፡ በዊአ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ቀሳውስት ። ወዲያቆናት ።

፶፩ ፤ ወእሉ ፡ እንዘ ፡ ከማነ ፡ ለባስያነ ፡ ሥጋ ፡ እሙንቱ ፡ ተመሰሉ ፡ ከመ ፡ መላእክት ፡ በሕይወቶሙ ፡ አንጽሑ ፡ ነፍሶሙ ፡ ወአፃዕደዉ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ወኢያርኰሱ ፡ ምኲራበ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ወተጽሕፈ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ በደሙ ፡ በግዑ ።

፶፪ ፤ ንሕነኒ ፡ እለ ፡ ተወለድነ ፡ በሥጋ ፡ ከማሆሙ ፡ ብነ ፡ ፫ቱ ፡ ልደታት ። አሐቲ ፡ ጥምቀት ፡ ቅድስት ፡ እንተ ፡ ትሬስየነ ፡ አምሳለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወ፩ዱ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዘይሠሪ ፡ አበሳ ፡ ወኃጢአተ ። ወ፩ዱ ፡ አንብዕ ፡ ዘበንስሓ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምውስጥ ፡ በአምሳለ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ዘያቀርብ ፡ ንጹሐ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ። ወኵልነ ፡ እንዘ ፡ ንጹሓን ፡ ንሕፅብ ፡ ሥጋነ በማይ ።

፶፫ ፤ ወንኩን ፡ አምሳለ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በቃለ ፡ ቅዳሴ ፡ በበዕበዮሙ ፡ ወበበማኅበሮሙ ፡ በበነገዶሙ ፡ ወበበሠራዊቶሙ ፡ በበአስማቲሆሙ ፡ ወበበኍልቆሙ ። ቦ ፡ ዘይኬልሉ ፡ ወቦ ፡ ዘየዐውዱ ፡ ቦ ፡ ዘይየብቡ ፡ ወቦ ዘይዜምሩ ፡ ቦ ፡ ዘየአኵቱ ፡ ወቦ ፡ ዘይሴብሑ እለ ፡ ፮ቱ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ከመዝ ፡ ይብሉ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ። ፀባዖት ፡ ፍጹም ፡ ወንሕነኒ ፡ ንበል ፡ ምስሌሆሙ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡

፶ ፤ ለእኛ ፡ ከዚህ ፡ በአሸዋ ፡ የተሠራ ፡ ነፋሳት ፡ የሚነፍሱበት ፡ ፈሳሾች ፡ የሚገፉት ፡ ቤት ፡ ያለን ፡ አይደለም ። በላይ ፡ ያለች ፡ ነፃ ፡ የምታወጣ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ናት እንጂ ፡ አስቀድመው ፡ የጳጳሳት ፡ አለቆችና ፡ ጳጳሳት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናትም ፡ የገቡባት ።

፶፩ ፤ እሊህ ፡ እንደኛ ፡ ሥጋን ፡ የለበሱ ፡ ሲሆኑ ፡ ባነዋወራቸው ፡ መላእክትን ፡ መሰሉ ፡ ሰውነታቸውን ፡ አነጹ ። ልብሳቸውንም ፡ ነጭ ፡ አደረጉ ፤ የሥጋቸውንም ፡ አዳራሽነት ፡ አላሳደፉም ፤ ስማቸውም ፡ በበጉ ፡ ደም ፡ በሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተጻፈ ።

፶፪ ፤ እንደ ፡ እርሳቸው ፡ በሥጋ ፡ ተወልደን ፤ እኛም ፡ ሦስት ፡ ልደቶች ፡ አሉን ። አንዲቱ ፡ ክርስቶስን ፡ የምታስመስለን ፡ ቅድስት ፡ ጥምቀት ፡ ናት ። አንዱም ፡ በደልንና ፡ ኃጢአትን ፡ የሚያስተሠርይ ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋውና ፡ ደሙ ፡ ነው ። አንዱም ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያቀርብ ፡ ከሰውነት ፡ ውስጥ ፡ በዮርዳኖስ ፡ አምሳል ፡ የሚወጣ ፡ በንስሓ ፡ ያለ ፡ ዕንባ ፡ ነው ፡ እኛ ፡ ሁላችንም ፡ ንጹሓን ፡ ስንሆን ፡ ሥጋችንን ፡ በንጹሕ ፡ ውኃ ፡ እንጠብ ።

፶፫ ፤ በምስጋና ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደሚያመሰግኑት ፡ መላእክት ፡ እንሁን ። በየማዕርጋቸውና ፡ በየማኅበራቸው ፡ በየነገዳቸውና ፡ በየሠራዊታቸው ፡ በየስማቸው ፡ በየቍጥራቸውም ፡ የሚጋርዱ ፡ አሉ ። የሚከቡም ፡ አሉ ። በዜማ ፡ የሚያመሰግኑ ፡ አሉ ። የሚዘምሩም ፡ አሉ ። በልብ ፡ የሚያመሰግኑ ፡ አሉ ። የሚዘምሩም ፡ አሉ ። በልብ ፡ የሚያመሰግኑ ፡ አሉ ። በቃል ፡ የሚያመሰግኑ ፡ አሉ ። ክንፎቻቸው ፡ ስድስት ፡ የሆኑት ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍጹም ፡ አሸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኛም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍጹም ፡ አሸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንበል ።

፶፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ አውሥኡ ።
ይ ፡ ሕ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ጸባዖት ፡ ፍጹም ፡ ምሉዕ ፡ ሰማ
ያተ ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ ፡ ስብሓቲከ።

፶፭ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ንዑ፡ናዕብዮ፡ንዑ፡ንወድሳ ፡
ንዑ ፡ ናክብራ ፡ ንዑ ፡ ናብዕላ ፡ ለበዐረ፡
በዓላት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሰንበተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ቅድስት ፡ ወንበል ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡
እንተ ፡ ገብረ እግዚአብሔር ፡ ንትፌሣሕ ፡
ወንትሐሠይ ፡ ባቲ ፡ ወንዘምር ፡ ምስለ ፡
አሳፍ ፡ ነቢይ ፡ እንዘ ፡ ንብል ፡ ተፈሥሑ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ዘረድአነ ።

፶፮ ፡ በአማን ፡ ንትፌሣሕ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ዘጸገወነ ፡ እምግብረ ግብርናት ግዕዛነ ፡
ወእምጽልመት ፡ ብርሃነ ። ወየብቡ ፡ ለአ
ምላከ ፡ ያዕቆብ ።
፶፯ ፡ በአማን ፡ ንየብብ ፡ ለአምላክ ፡ ነቢ
ያት ፡ ቅዱሳን ፡ ወለእግዚአ ፡ ሐዋርያት ፡
ንጹሓን ። ንሥኡ ፡ መዝሙረ ፡ ወሀቡ ፡
ከበሮ ።
፶፰ ፤ በአማንኬ ፡ ንንሣእ ፡ ወንጌለ ፡
ዘቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ትሕትና ፡ ወፍቅር ። ወን
ኅድግ ፡ ኦሪተ ፡ ዘቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ፍትሕ ፡
ወቀትል ፡ ቤዛ ፡ ነፍስ ፡ ህየንተ ፡ ነፍስ ።
መዝሙር ፡ ሐዋዝ ፡ ዘምስለ ፡ መሰንቆ ፡
ትእዛዝ ፡ ወንጌልኬ፡ ሠናይ ፡ ምስለ ፡ ገቢ
ሮቱ ።
፶፱ ፤ መሰንቆ ፡ ይእቲ ፡ ሃይማኖት ፡ እንተ
ለብስዋ ፡ ሰማዕት ፡ ንፍሑ ፡ ቀርነ ፡ በዕ
ለተ ፡ ሠርቅ ።
፷ ፡ በአማን ፡ ንበል ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ በመዝ
ሙረ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ በእምርት ፡ ዕለት ፡
በዓልነ ። በአማን ፡ እምርት ፡ ይእቲ ፡
እንተ ፡ ባቲ ፡ አኀዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ፡
ይግበር ፡ ግብሮ ።
፷፩ ፡ አ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ ቀዳማዊት ፡ ይእቲ
ወአኮ ፡ ደኃራዊት ። አ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ ደኃ
ራዊት ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ ትሰፍን ፡ ለዓለም ።

፷፪ ፡ አ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ ለአብርሃም ፡ ተከ
ሥተት ፡ ወከሠየሁ ፡ አመነየት ፡ ወአነበየት ፡
ወኪያሁ ፡ አስተፍሥሐት ።

፶፬ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ተሰጥዎውን ፡ መልሱ ።
ይ ፡ ሕ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍጹም ፡
አሸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ የጌትነትህ ፡ ምስ
ጋና ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ የመላ ፡ ነው ።

፶፭ ፡ ይ ፡ ካ ፡ የበዓላትን ፡ በኵር ፡ ኑ ፡
ከፍ ፡ ከፍ ፡ እናድርጋት ። ኑ ፡ እናመስግናት ፡
ኑ ፡ እናክብራት ። ኑ ፡ በዓል ፡ እናድርጋት ፡
ይህችውም ፡ ቅድስት ፡ ሰንበተ ፡ ክርስቲያን
ናት ። ይህች ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡
የሠራባት ፡ ናት ፡ እንበል ። በርሷም ፡ ደስ ፡
ይበለን ፡ ኀሤትም ፡ እናድርግ ፤ እንደ ፡
ነቢዩ ፡ እንደ ፡ አሳፍም ፡ በረዳን ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ደስ፡ይበላችሁ፡እያልን፡እንዘምር ።
፶፮ ፤ ከመገዛት ፡ ነፃነትን ፡ ከጨለማም ፡
ብርሃንን ፡ በሰጠን ፡ በእግዚአብሔር ፡ በዕ
ውነት ፡ ደስ ፡ ይበለን ። ለያዕቆብ ፡ አምላክ ፡
እልል ፡ በሉ ።
፶፯ ፡ ለክቡራን ፡ ነቢያት ፡ አምላክ ፡ ለን
ጹሓን ፡ ሐዋርያትም ፡ ጌታ ፡ በዕውነቱ ፡
እልል ፡ እንበል ፡ በገናን ፡ ያዙ ፡ ከበሮንም ፡
ስጡ ።
፶፰ ፤ ወንጌልን ፡ በዕውነት ፡ እንያዝ ፡
በውስጡ ፡ ትሕትናና ፡ ፍቅር ፡ ያለበትን ፡
ኦሪትን ፡ ግን ፡ እንተው ፤ በውስጡ ፡ ስለነ
ፍስ ፡ የነፍስ ፡ ቤዛ ፡ የሚሆን ፡ የሞት ፡
ፍርድ ፡ ያለበትን ፡ በገና ፡ ከመሰንቆ ፡ ጋራ ፡
የተስማማ ፡ ነው ፤ የወንጌልም ፡ ትእዛዝ ፡
ከመሥራቱ ፡ ጋራ ፡ ያማረ ፡ ነው ።
፶፱ ፤ መሰንቆ ፡ ሰማዕታት ፡ የለበሷት ፡
ሃይማኖት ፡ ናት ። በመባቻ ፡ ቀን ፡ ነጋሪት ፡
ምቱ ።
፷ ፡ በነቢዩ ፡ በዳዊት ፡ መዝሙር ፡ በታ
ወቀች ፡ በበዓላችን ፡ ቀን ፡ በዕውነት ፡ ሃሌ ፡
ሉያ ፡ እንበል ። እግዚአብሔር ፡ ሥራውን ፡
ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የጀመረባት ፡ በዕውነት ፡
የታወቀች ፡ ናት ።
፷፩ ፤ ወዮ ፡ ይህች ፡ ዕለት ፡ ቀዳሚት ፡
ናት ፡ ደኃራዊት ፡ አይደለችም ። ወዮ ፡
ይህች ፡ ዕለት ፡ ለዘላለሙ ፡ የምትገዛ ፡ ደኃ
ራዊት ፡ ናት ።
፷፪ ፤ ወዮ ፡ ይህች ፡ ዕለት ፡ ለአብርሃም ፡
ተገለጸች ። እርሱንም ፡ አስመኘች ፤ ትንቢ
ትም ፡ አናገረች ፤ እርሱንም ፡ ደስ ፡ አሰኘች ።

፳፫ ፤ ኦ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ ለሙሴ ፡ በደብረ ፡
ሲና ፡ ተከሥተት ፡ ወእምኀበ ፡ እስራኤል ፡
ተከብተት ።

፳፬ ፤ ኦ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ በነቢያት ፡ ተዐ
ውቀት ፡ ወእምኀበ ፡ ሕዝበ ፡ አይሁድ ፡
ተሠወረት ። በኀቤነሰ ፡ ፍጹመ ፡ አስተርአ
አየት ፤ ወከመ ፡ ፀሓይ ፡ አንበስበሰት ፡ ለለ
ሰሙኑ ፡ ትሰፍን ፡ ወለለሰሙኑ ፡ ትነግሥ ፡
ወለለሰሙኑ ፡ ትትቀመር ።

፳፭ ፤ ኦ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ ቅድስቱ ፡ ለአብ ፤
ቡርክቱ ፡ ለወልድ ፤ ልዕልቱ ፡ ለመንፈስ ፡
ቅዱስ ። ንትፈሣሕ ፡ ባቲ ፡ ወንትሐሠይ ፡
ባቲ ፤ ቀድስዋ ፡ ከመ ፡ ትትቀደሱ ፡ ባቲ ።

፳፮ ፤ ኦ ፡ ባዕዳት ፡ ዕለታት ፡ እንተ ፡ ባቲ
ተአመርክን ፡ ለአዝማን ፡ ወለመዋዕል ፤
ንዓኬ ፡ ውድሳሃ ፡ ለበዓለ ፡ በዓላት ፡ እንተ ፡
ይእቲ ፡ ሰንበተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ።

፳፯ ፤ ኦ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡
ብሊት ፡ ተፀርዐት ፡ ወሐዳስ ፡ ጸንዐት ። ኦ ፡
ዛቲ ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ሙቁሓን ፡ ተፈ
ትሑ ፡ ወአግብርት ፡ ግዕዙ ።

፳፰ ፤ ኦ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡
ምዝቡር ፡ ተሐንጸ ፡ ወሰይጣን ፡ ተኀጕለ ፡

፳፱ ፤ ወካዕበ ፡ አመ ፡ ትሰፍን ፡ ዛቲ ፡
ዕለት ፡ ይከውን ፡ ሐዲስ ፡ ግብር ፡ ወሐ
ዲስ ፡ ነገር ፡ አልቦ ፡ አሜሃ ፡ ብርሃነ ፡
ፀሓይ ፡ ወወርኅ ፡ ወከዋክብት ፡ ኢዋካ ፡
ወኢፀዳል ፡ ኢክረምት ፡ ወኢሐጋይ ።

፴ ፤ ወታስተናፍስ ፡ ምድር ፡ ፯ተ ፡ ዕለ
ታተ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ውስ
ቴታ ፡ ዘነፍስ ፡ ሕያው ። ወይትፌኖ ፡ ቃል ፡
ከመ ፡ ፋፃ ፡ ቀጢን ፡ ወበይእቲ ፡ ቃል ፡ ይት
አተት ፡ ጽንዐ ፡ ሰማያት ፡ ወያድለቀልቅ ፡
ግዘፈ ፡ ምድር ።

፴፩ ፤ አሜሃ ፡ መቃብራት ፡ ይትከሠታ ፡
ወሙታን ፡ እለ ፡ በልዩ ፡ ዘእምዓለም ፡ ይት
ነሥኡ ፡ ከመ ፡ ቅጽበተ ፡ ዓይን ። ወያወፊ ፡
አብ ፡ ለወልዱ ፡ መንግሥተ ፡ ወምኵናነ ፡
አሜሃ ፡ ያስተርኢ ፡ ኃይለ ፡ መብረቅ ፡
ሐዲስ ፡ ወቃለ ፡ ነጐድጓድ ፡ ግሩም ፡ እም
ቀዳሚ ፡ ዘኢሰምዐ ፡ እዝን ፡ ወዘኢርእየ ፡
ዓይን ።

፳፫ ፤ ወዮ ፡ ይህች ፡ ዕለት ፡ ለሙሴ ፡ በደ
ብረ ፡ ሲና ፡ ተገለጸች ፡ ከእስራኤል ፡ ግን ፡
ተሠወረች ።

፳፬ ፤ ወዮ ፡ ይህች ፡ ዕለት ፡ በነቢያት ፡
ታወቀች ። ከአይሁድ ፡ ወገንም ፡ ተሠወ
ረች ። ብኛ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ ተገለጸች
እንደ ፡ ፀሐይም ፡ ተመላለሰች ፡ በየሳምንቱ፡
ትሰለጥናለች ፤ በየሳምንቱ ፡ ትነግሣለች ፡
በየሳምንቱ ፡ ትቆጠራለች ።

፳፭ ፤ ወዮ ፡ ይህች ፡ ዕለት ፡ አብ ፡ የቀ
ደሳት ፡ ወልድ ፡ የባረካት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ
ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረጋት ፡ ናት ። በርሷ ፡ ደስ ፡
ይበለን ። በርስዋም ፡ ኀሤት ፡ እናድርግ ።
ትከብሩባት ፡ ዘንድ ፡ አክብሯት ።

፳፮ ፤ ዘመን ፡ ወር ፡ ለመባል ፡ በርሷ ፡
የታወቃችሁ፡ሌሎች ፡ ዕለታት ፡ ሆይ ፡ የበ
ዓላትን ፡ በዓር ፡ ኑ ፡ አመስግኗት ። ይህች
ውም ፡ የከበረች ፡ ሰንበተ ፡ ክርስቲያን ፡
ናት ።

፳፯ ፤ ወዮ ፡ ይህች ፡ ዕለት ፡ ያረጀችዋ ፡
ያለፈችባት ፡ አዲሲቱ ፡ የጸናችባት ፡ ናት ።
ወዮ ፡ ይህች ፡ ዕለት ፡ እስረኞች ፡ (ነፍሳት ፡)
የተፈቱባት ፡ ባሮች ፡ ነፃ ፡ የወጡባት ፡ ናት።

፳፰ ፤ ወዮ ፡ ይህች ፡ ዕለት ፡ የፈረሰ ፡ የታ
ነጸባት ፡ ሰይጣንም ፡ የጠፋባት ፡ ናት ።

፳፱ ፤ ዳግመኛም ፡ ይህች ፡ ዕለት ፡ በምት
ሠለጥንበት ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ አዲስ ፡
ነገርም ፡ ይሆናል ። ያን ፡ ጊዜ ፡ የፀሐይና ፡
የጨረቃ ፡ የከዋክብትም ፡ ብርሃን ፤ ወይም ፡
ፀዳል ፡ ክረምት ፡ ወይም ፡ በጋ ፡ የለም ።

፴ ፤ በውስጧ ፡ በነፍስ ፡ ሕያው ፡ ሁኖ ፡
የሚንቀሳቀስ ፡ ፍጥረት ፡ ሳይኖርባት ፡
ምድር ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ታርፋለች ፤ እንደ ፡
ረቂቅ ፡ ፉጨት ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ይላካል ፤ በዚ
ያችም ፡ ቃል ፡ የሰማያት ፡ ጽንዕ ፡ ይወገዳል
የምድርም ፡ ግዘፍ ፡ ይነዋወጻል ።

፴፩ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ መቃብራት ፡ ይከፈ
ታሉ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ የፈረሱ፡
ሙታን ፡ ፈጥነው ፡ እንደ ፡ ዓይን ፡ ቅጽበት ፡
ይነሣሉ ። አብ ፡ መንግሥቱንና ፡ ፍርዱን ፡
ለልጁ ፡ ይሰጣል ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ የመ
ብረቅ ፡ ኃይል ፡ ይታያል ። ግሩም ፡ የሚሆን
የነጐድጓድም ፡ ቃል ፡ ይሰማል ። ከመጀ
መሪያ ፡ (ከጥንት ፡) ጀምሮ ፡ ጆሮ ፡ ያልሰ
ማው ፡ ዓይንም ፡ ያላየው ።

፸፪ ፤ ወይቀውሙ ፡ ቅድሜሁ ፡ ግሩማን ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ አክናፈ ፡ እሳት ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ስም ፡ ወኢይብልዎሙ ፡ ዕገሌ ፡ ወዕገሌ ፡ ወእለ ፡ ነበሩ ፡ ውስተ ፡ መንጦላ ዕቱ ፡ ለአብ ፡ መላእክተ ፡ ገጽ ፡ እሙንቱ ። ወዘእሉ ፡ ክንፍ ፡ ይትኃዳዕ ፡ ምስለ ፡ ክንፍ ፡ ይደምፁ ፡ ወያንጐደጕዱ ፡ ወይመልኁ ፡ ሰይፎሙ ፡ ወያንበለብሉ ፡ ከመ ፡ ያርእዩ ፡ ጽንዖሙ ።

፸፫ ፤ አሜሃ ፡ ትትከሠት ፡ ባሕረ ፡ እሳት ፡ እስከ ፡ ማዕምቅቲሃ ፡ ወግበ ፡ አስሐትያ ፡ ዘመትሕቴሃ ፡ ወፈለገ ፡ እሳት ፡ ይውኅዝ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ ኵሉ ፡ ዘጽኑሕ ፡ ሎቱ ።

፸፬ ፤ አሜሃ ፡ መጻሕፍት ፡ ይትከሠታ ፡ ወምግባራት ፡ ይሰጣሕ ፡ ወልሳን ፡ ያረምም፡ ወአፍ ፡ ብቅው ፡ ይብሕም ፡ ወይቀውም ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ፡ ወበ ዓቢይ ፡ ጸጥ ። ወኢተአክል ፡ ኵላ ፡ ምድር ፡ ዘእንበለ ፡ መጠነ ፡ ምክያደ ፡ እግር ፡ ወይጸ ዐቅ ፡ ከመ ፡ ጽፍቀተ ፡ ሮማን ።

፸፭ ፤ አልቦ ፡ አሜሃ ፡ ሐፂር ፡ ወነዊኅ ፡ ጸሊም ፡ ወቀይሕ ፡ አላ ፡ ፩ዱ ፡ አካል ፡ ወ፩ዱ ፡ ኅብር ።

፸፮ ፤ አልቦ ፡ አሜሃ ፡ ቤዛ ፡ ነፍስ ፡ ወኢ ተውላጠ ፡ ብእሲ ፡ በብእሲቱ ፡ አብ ፡ በወ ልዱ ፡ ወእም ፡ በወለታ፡ አላ ፡ ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ ይነሥእ ፡ ፍዳ ፡ ምግባሩ ።

፸፯ ፤ ኢየኀፍሮ ፡ ለባዕል ፡ እንበይነ ፡ ብዕሉ ፡ አላ ፡ በከመ ፡ ተሐሰበ ፡ ሎቱ ፡ ወኢ ይምሕሮ ፡ ለነዳይ ፡ እንበይነ ፡ ንዴቱ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ መሥመሬ ፡ ሎቱ ።

፸፰ ፤ አሜሃ ፡ ጻድቃን ፡ ይትፌሥሑ ፡ እስመ ፡ ለሐዉ ፡ በሕይወቶሙ ፡ ወኃጥኣን ፡ ይበክዩ ፡ እስመ ፡ አፍቀሩ ፡ ሠሐቀ ፡ ወሥ ላቀ ፤ እስመ ፡ በጽሐቶሙ ፡ ዕለተ ፡ ፍዳ ፡ ወደይን ።

፸፪ ፤ የእሳት ፡ ክንፎች ፡ ያሏቸው ፡ ግሩ ማን ፡ መላእክት ፡ በፊቱ ፡ ይቆማሉ ፤ ስም ፡ የሌላቸው ፡ ዕገሌና ፡ ዕገሌ ፡ የማይሏቸው ፡ በአብ ፡ መጋረጃ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ባለ ሟሎች ፡ መላእክት ፡ ናቸው ። የሊህም ፡ ክንፍ ፡ ከክንፍ ፡ ጋራ ፡ ይሳበቃል ፤ ይሰ ማሉ ፤ ያንጐደጕዳሉ ፤ ሰይፋቸውንም ፡ ይመዛሉ ፤ ጽናታቸውንም ፡ የሳዩ ፡ ዘንድ ፡ ይበራሉ ።

፸፫ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ የእሳት ፡ ባሕር ፡ እስከ ፡ መሠረቷ ፡ ትገለጣለች ። በበታቿ ፡ ያለ ፡ የው ርጭ ፡ ጉድጓድም ፡ የእሳት ፡ ወንዝም ፡ ይፈሳል ። ሁሉ ፡ ትጠብቆለት ፡ ያለውን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ።

፸፬ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ መጻሕፍት ፡ ይገለጣሉ ፡ ሥራም ፡ ይገለጣል ፤ አንደበትም ፡ ዝም ፡ ይላል ፡ የተከፈተ ፡ አፍም ፡ ድዳ ፡ ይሆናል ። ፍጥረቱም ፡ ሁሉ ፡ በመፍራት ፡ በመንቀጥ ቀጥ ፡ በታላቅ ፡ ጸጥታም ፡ ይቆማል ። ምድር ፡ ሁላ ፡ ከእግር ፡ መሄጃ ፡ ልክ ፡ በቀር አትበቃም ፤ እንደ ፡ ጽፍቀተ ፡ ሮማን ፡ ይጨናነቃል ።

፸፭ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ አጭርና ፡ ረጅም ፡ ቀይና ፡ ጥቁር ፡ የለም ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ መልክ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፸፮ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ የነፍስ ፡ ቤዛ ፡ የለም ፡ ወንድ ፡ በሚስቱ ፡ መለወጥም ፡ ቢሆን ፡ አባት ፡ በልጁ ፡ እናትም ፡ በልጅዋ ፡ አን ዱም ፡ አንዱ ፡ የሥራውን ፡ ፍዳ ፡ ይቀበላል እንጂ ።

፸፯ ፤ ባለጸጋውን ፡ ስለባለጸግነቱ ፡ አያ ፍረውም ። እንደ ፡ ተገመገመለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለድኃውም ፡ ስለ ፡ ድኅነቱ ፡ አይራ ራለትም ፡ እርሱን ፡ ደስ ፡ ካላሰኘው ።

፸፰ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጻድቃን ፡ ደስ ፡ ይላቸ ቸዋል ፡ በሕይወታቸው ፡ አልቅሰዋልና ። ኃጥአንም ፡ ያለቅሳሉ ፡ ሣቅንና ፡ ሥላቅን ፡ ስለ ፡ ወደዱ ፡ የፍርድና ፡ የፍዳ ፡ ቀን ፡ ደርሳ ባቸዋለችና ።

፸፱ ፤ አሜሃ ፡ ብዑላን ፡ ይነድዩ ፡ እስመ ፡ ሠለጡ ፡ ትፍግዕቶሙ ፡ በዐመፃ ፡ ወነዳያን ፡ ይብዕሉ ፡ እስመ ፡ ተወክፉ ፡ ንዴቶሙ ፡ በአኰቴት ።

፹ ፤ ርኁባን ፡ ይጸግቡ ፡ እስመ ፡ ተጸነሱ ፡ በሕይወቶሙ ።

፹፩ ፤ አሜሃ ፡ ነባብያን ፡ ያረምሙ ፡ እስመ ፡ ተናገሩ ፡ ከንቶ ፡ ወበከ ፡ ወዕጉሣን ፡ ይነብቡ ፡ እስመ ፡ ኢነደግዎ ፡ ለልሳኖሙ ፡ ይሩጽ ፡ ውስተ ፡ ሐሜት ፡ ወኢያኀዘኑ ፡ ቢጾሙ ፡ ፍጹመ ።

፹፪ ፤ አሜሃ ፡ ጽኑዓን ፡ ይደክሙ ፡ እስመ አኀለቁ ፡ ሥጋሆሙ ፡ በዝሙት ፡ ወድኩማን ፡ ይጸንዑ ፡ እስመ ፡ አድከሙ ፡ ኃይሎሙ ፡ በሰጊድ ፡ ወበትጋህ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ።

፹፫ ፤ አሜሃ ፡ ኃያላን ፡ ይፀብሱ ፡ እስመ ፡ ሰፍሑ ፡ እደዊሆሙ ፡ ውስተ ፡ ትዕግልት ፡ ወአብከዩ ፡ እቤረ ፡ ወዕጓለ ፡ ማውታ ።

፹፬ ፤ አሜሃ ፡ ምኑናን ፡ ይሠርሩ ፡ ከመ ፡ አንሥርት ፡ ወይሠርዕ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ወይትሐደስ ፡ ውርዙቶሙ ።

፹፭ ፤ ዕቡያን ፡ ወዝኁራን ፡ ይትቀፈጹ ፡ ወይትከሠት ፡ ኀፍረቶሙ ።

፹፮ ፤ አሜሃ ፡ ዕሩቃን ፡ ይለብሱ ፡ እስመ ፡ አርሐሰሙ ፡ ነፍኒፈ ፡ ዝናም ፡ ወጠል ፡ ወአመንደቦሙ ፡ ቊር ፡ ወአስሐትያ ፡ ወአውዐዮሙ ፡ ሐሩረ ፡ ፀሓይ ።

፹፯ ፤ አልቦ ፡ አሜሃ ፡ ኲናት ፡ ወወልታ ፡ ቀስት ፡ ወሐፅ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘበምድር ፡ ተሰዕረ ።

፹፰ ፤ አሜሃ ፡ ይፈትሕ ፡ ንጉሥ ፡ በኵነኔ ፤ ርትዕ ፡ ዘአልቦ ፡ አድልዎ ።

፹፱ ፤ አሜሃ ፡ ይትፈለጡ ፡ ኃጥኣን ፡ እማዕከለ ፡ ጻድቃን ፡ ወይትሌለዩ ፡ ርኵሳን ፡ እማዕከለ ፡ ንጹሓን ።

፺ ፤ ምንትኬ ፡ ዘአሜሃ ፡ ዐውያት ፡ ወዘአሜሃ ፡ ክላሕ ፡ ወዘአሜሃ ፡ አንብዕ ፡ እስከ ፡ ለሊሁ ፡ ፈጣሪ ፡ ያነብዕ ፡ በእንተ ፡ ፍጥረቱ ፡ እንተ ፡ ለሐኰት ፡ እዴሁ ፡ ሶበ ፡ ይሬእዮሙ እንዘ ፡ የሐውሩ ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ኀጕል ።

፸፱ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ባለጸጎች ፡ ይደኸያሉ ፡ ተድላ ፡ ደስታቸውን ፡ በዐመፅ ፡ ጨርሰዋልና ፡ ነዳያንም ፡ ባለጸጎች ፡ ይሆናሉ ፡ ንዴታቸውን ፡ በምስጋና ፡ ተቀብለዋልና ።

፹ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተርበው ፡ የነበሩ ፡ ይጸግባሉ ፡ በሕይወታቸው፡ተቸግረው፡ነበሩና።

፹፩ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተናጋሪዎች ፡ የነበሩ ፡ ዝም ፡ ይላሉ ፤ ከንቱንና ፡ ብላሽን ፡ ነገር ፡ ተናግረዋልና ። ትዕግሥተኞች ፡ የነበሩ ፡ ይናገራሉ ። አንደበታቸውን ፡ ወደ ፡ ሐሜት ይሮጥ ፡ ዘንድ ፡ አልተዉትምና ፤ ባልንጀራቸውንም ፡ ፈጽሞ ፡ አላሳዘኑምና ።

፹፪ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጽኑዓን ፡ የነበሩ ፡ ይደክማሉ ፤ ሥጋቸውን ፡ በዝሙት ፡ አድክመዋልና ፡ ደክመው ፡ የነበሩት ፡ ይጸናሉ ፡ ኃይላቸውን ፡ በሰጊድ ፡ በመዓልትና ፡ በሌሊትም ፡ በመትጋት ፡ አድክመዋልና ።

፹፫ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኃያላን ፡ ልምሾ ፡ ይሆናሉ ፡ እጃቸውን ፡ ለመቀማት ፡ ዘርግተዋልና ። ባልቴትንና ፡ አባት ፡ እናት ፡ የሞቱበትን ፡ አስለቅሰዋልና ።

፹፬ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ የተናቁት ፡ እንደ ፡ አንሥርት ፡ ይበራሉ ፤ ክንፋቸውም ይጨጣል ፤ ጕልማስነታቸውም ፡ ይታደሳል ።

፹፭ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ትዕቢተኞችና ፡ ኵሮች ይገለጻሉ ፡ ኀፍረታቸውም ፡ ይገለጻል ።

፹፮ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የታረዙት ፡ ይለብሳሉ ፡ የዝናምና ፡ የጠል ፡ ካፊያ ፡ አርሷቸዋልና ፤ ብርድና ፡ ውርጭ ፡ አስቸግሯቸዋልና ፤ የፀሓይ ፡ ሐሩርም ፡ አቃጥሏቸው ፡ ነበርና ።

፹፯ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጦርና ፡ ጋሻ ፤ ቀስትና ፡ ፍላፃ ፡ የለም ፡ በምድር ፡ የነበረ ሁሉ ፡ ተሽሯልና ።

፹፰ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ አድልዎ ፡ በሌለበት ፡ በቅን ፡ ፍርድ ፡ ይፈርዳል ።

፹፱ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኃጥኣን ፡ ከጻድቃን ፡ መካከል ፡ ይለያሉ ፡ ርኵሳንም ፡ ከንጹሓን ፡ መካከል ፡ ይለያሉ ።

፺ ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዐውያት ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጩኸት ፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ልቅሶ ፡ ምን ፡ ያህላል ፤ እርሱ ፡ ቅሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ መንገድ ፡ ሲሄድ ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ እጁ ፡ ስለ ፡ ፈጠራቸው ፡ ፍጥረቶቹ ፡ እስኪያለቅስ ፡ ድረስ ።

፺፩ ፤ አሚሃ ፡ ኃጥአን ፡ ይበክዩ ፡ በእንተ ፡ ርእሶሙ ፡ ወጻድቃን ፡ ይበክዩ ፡ በእንተ ፡ ዘመዶሙ ። ወመላእክተ ፡ ሰማይ ፡ የኀዝኑ ፡ በእንተ ፤ ፍጥረተ ፡ ሰብእ ።

፺፪ ፡ በዝየ ፡ ይዑድ ፡ ንፍቅ ፡ ቀሲስ ።

፺፫ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ወሶበ ፡ ተፈጸመ ፡ ኵሉ ፡ አሚሃ ፡ ለእሊአሁ ፡ ለኅሩያኒሁ ፡ ወለጻድቃኒሁ ፡ ደብተራ ፡ ብርሃን ፡ ይተከል ፡ ወመንጦላዕተ ፡ እሳት ፡ ይሰፋሕ ፡ ዘቦ ፡ ፯ቱ ፡ ምሥዋር ።

፺፬ ፤ ወህየ ፡ ይበውእ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ውስተ ፡ ምሥጢር ፡ ለሥርዓተ ፡ ግብር ፡ ወያቀውሞሙ ፡ ለካህናት ፡ በየማኑ ፡ ወለዲያቆናት ፡ በጾጋሙ ፡ ከመ ፡ ያርእዮሙ ፡ ሥርዓተ ፡ ምሥጢር ።

፺፭ ፤ ምንተ ፡ ይመስል ፡ ወምንት ፡ ስሙ ፡ ወምንተ ፡ ይትበሀል ፡ ዘአሚሃ ፡ ምሥጢር ፡ ወይትከሀል ፡ ይእዜ ፡ ይንግርዎ ፡ ወኢሀሎ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

፺፮ ፤ አ ፡ ካህናት ፡ ሥዩማን ፡ ክብር ፡ ለክሙ ፡ ሶበ ፡ ትትከሀኑ ፡ ምስለ ፡ እግዚአ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ።

፺፯ ፤ አ፡ዲያቆናት ፡ ኅሩያን፡ እለ፡ትመስሉ አስራበ ፡ ወርቅ ፡ ንጹሕ ፡ ሥፍሓ ፡ ለክሙ ፡ ሶበ ፡ ትሬእዩ ፡ ምሥጢረ ፡ ዕፁብ ።

፺፰ ፤ አ ፡ ቅዱሳን ፡ አበው ፡ እለ ፡ ትመስሉ ፡ አዕማደ ፡ ወርቅ ፡ ንጹሕ ፡ ዘቅውም ፡ ዲበ ፡ ዕብነ ፡ ሰንፔር ፡ ብፅዓን ፡ ለክሙ ።

፺፱ ፤ አ ፡ ኵልክሙ ፡ መሃይማናን ፡ እለ ፡ ትመስሉ ፡ ከዋክብተ ፡ ብሩሃን ፡ ዕበይ ፡ ለክሙ ፡ ሶበ ፡ ትበውኡ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ከብካበ ፡ መርዓሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዕበይ ፡ ለክ ሙ ፡ ሶበ ፡ ትሬእይዎ ፡ ለእግዚእክሙ ፡ ይቀንት ፡ ወያንሶሱ ፡ ምስሌክሙ ፡ ወይሜጥወክሙ ፡ ዘዚአሁ ፡ ሀብታተ ።

፻ ፤ አሚሃ ፡ ስአሉ ፡ ለነ ፡ አስተምሕሩ ፡ በእንቲአነ ፡ ከመ ፡ ይምሐረነ ፡ ወይሣሃለነ ፡ አኮ ፡ በሥንነ ፡ አላ ፡ በሥንክሙ ፡ አኮ ፡ በከመ ፡ ምግባሪነ ፡ ርኵስት ፡ አላ ፡ በከመ ፡ ምሕረቱ ፡ ለአምላክነ ።

፺፩ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኃጥአን ፡ ስለ ፡ ራሳቸው፡ ያለቅሳሉ ፡ ጻድቃንም ፡ ስለ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ያለቅሳሉ ፤ የሰማይ ፡ መላእክትም ፡ ስለ ፡ ፍጥረት ፡ ያዝናሉ ።

፺፪ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንፍቅ ፡ ቄስ ፡ ማዕጠንቱን ፡ ይዞ ፡ ይዞር ።

፺፫ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ሁሉ ፤ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ለመረጣቸው ፡ ለወዳጆቹ ፡ ለጻድቃኖቹ ፡ የብርሃን ፡ ድንኳን ፡ ይተከላል ፡ ሰባት ፡ መሠወሪያ ፡ ያለው ፡የእሳት፡መጋረጃ ፡ ይዘረጋል ።

፺፬ ፤ የካህናት ፡ አለቃ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከዚያ ፡ ወደዚህ ፡ ምሥጢር ፡ ይገባል ። ለግብር ፡ ሥራት ፡ ቀሳውስትን ፡ በቀኙ ፡ ዲያቆናትንም ፡ በግራው ፡ ያቆማቸዋል ፤ የምሥጢርን ፡ ሥራት ፡ ያሳያቸው ፡ ዘንድ ።

፺፭ ፤ ምን ፡ ይመስላል ፤ ስሙስ ፡ ምንድን ፡ ነው ፤ የዚያን ፡ ጊዜውስ ፡ ምሥጢር ፡ምን ፡ ይባላል ። ዛሬ ፡ ሊናገሩት ፡ አይቻልም ። በሰው ፡ ልቡናም ፡ የለም ።

፺፮ ፤ የተሾማችሁ ፡ ካህናት ፡ ሆይ ፡ ከሰማይና ፡ ከምድር ፡ ጌታ ፡ ጋራ ፡ ካገለገላችሁ ፡ ለናንት ፡ ክብር ፡ ይገባችኋል ።

፺፯ ፤ የንጹሕ ፡ ወርቅ ፡ ሻሻቴ ፡ የምትመስሉ ፡ የተመረጣችሁ ፡ ዲያቆናት ፡ ሆይ ፡ ለናንተ ፡ ደስታ ፡ ይገባል ። ድንቅ ፡ ምሥጢርን ፡ ባያችሁ ፡ ጊዜ ።

፺፰ ፤ ሰንፔር ፡ በሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ላይ ፡ የቆመ ፡ የንጹሕ ፡ ወርቅ ፡ አዕማድን ፡ የምትመስሉ ፡ ክቡራን ፡ አበው ፡ ሆይ ፡ መመስገን ፡ ይገባችኋል ።

፺፱ ፤ ብሩሃን ፡ ከዋክብትን ፡ የምትመስሉ ፡ ሁላችሁ ፡ ምእመናን ፡ ሆይ ፡ ለናንተ ፡ ክብር ፡ ይገባል ። ክርስቶስ፡ አንድነትን ፡ ወደሚያደርግባት ፡ ወደዚያች ፡ ሠርግ ። በምትገቡበት ፡ ጊዜ ። ጌታችሁን ፡ ታጥቆ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ እየተመላለሰ ፡ የርሱን ፡ ሀብት ፡ ሲሰጣችሁ ፡ ባያችሁት ፡ ጊዜ ፡ ለናንተ ፡ ክብር ፡ ይገባል ።

፻ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ለኛ ፡ ለምኑልን ፤ ስለኛ ፡ አማልዱ ፤ ይምረን ፡ ይቅርም ፡ ይለን ፡ ዘንድ በሥራችን ፡ አይደለም ፤ በሥራችሁ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በረከሰች ፡ ሥራችን ፡ አይደለም ፡ እንደ ፡ አምላካችን ፡ ምሕረት ፡ ነው ፡ እንጂ

፻፩ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፡ ወአኮ ፡ በከመ ፡ አበሳነ ፡ ይ ፡ ቀ ፡ ጊዜ ፡

፻፪ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ንስእለከ ፡ እግዚኦ ፡ ወናስተበቍዐከ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ አበዊነ ፡ ወአኀዊነ ፡ ወፈለሱ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኀላፊ ፡ ከመ ፡ ታዕርፎሙ ፡ ሠናየ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ንጹሕ ፡ እምርስሐት ፡ በቅድሜከ ፡ ሰብእሰ ፡ ዕቡረ ፡ ኃጢአት ፡ ውእቱ ።

፻፫ ፤ እመሰ ፡ ኃጢአተኑ ፡ ትትዐቀብ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚኦ ፡ መኑ ፡ ይቀውም ፡ ቅድሜከ ።

፻፬ ፤ ዮም ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ሰንበተ ፡ ብርሃን ፡ በነበ ፡ ተሠርዐ ፡ ሥጋከ ፡ ወደምከ ። እለ ፡ ነአምር ፡ አስማቲሆሙ ፡ ንዜክር ፡ በቃለ ፡ ዝንቱ ፡ ላእክ ፡ ወእለሂ ፡ ኢነአምር ፡ አስማቲሆሙ ፡ አንተ ፡ ተዘከሮሙ ፡ በምሕረትከ ። ወጸሐፍ ፡ ስሞሙ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አግዓዚት ።

፻፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ በእንተ ፡ ብፁዕ ።

፻፯ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ንፍቅ ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ።

፻፯ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፡ መሐሮሙ ፡ እግዚኦ ፡ ወተሣሃሎሙ ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጳጳሳት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወኵሎሙ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ።

፻፰ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ቅድመ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዳሴከ ፡ ስብሐት ፡ ወአኰቴት ፡ ዕበይ ፡ ወልዕልና ። ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ አልቦ ፡ መጠን ፡ ለዕበይከ ፡ ወአልቦ ፡ ማኅለቅት ፡ ለመንግሥትከ ፡ አልቦ ፡ ወሰን ፡ ለግዝዓትከ ፡ ወአልቦ ፡ ጽንፍ ፡ ለምልክናከ ።

፻፱ ፤ ኢይትአመር ፡ እምኀበ ፡ ይወዕእ ፡ መለኮትከ ፡ ወኀበ ፡ ይትዔለድ ፡ ህላዌከ ፡ ኢይጤየቅ ፡ እምኀበ ፡ ይውኅዝ ፡ መለኮትከ ፡ ወኀበ ፡ ይደነግግ ፡ ህላዌከ ።

፻፩ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ ምሰት ፡ ጊዜ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ብደላችን ፡ አይደለም ።

፻፪ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አቤቱ ፡ ኀላፊ ፡ ከሚሆን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡ ሄዱ ፡ (ስለ ፡ ሞቱ) ፡ አባቶቻችንና ፡ ስለ ፡ ወንድሞቻችን ፡ እንለምንሃለን ፡ እንማልድሃለንም ። በበጎ ፡ ታሳርፋቸው ፡ ዘንድ ፡ በፊትህ ፡ ከኃጢአት ፡ ንጹሕ ፡ የለምና ፡ ሰውስ ፡ በኃጢአት ፡ ጭቃ ፡ የሆነ ፡ ነው ።

፻፫ ፡ ኃጢአትን ፡ ብትጠባበቅ ፡ ግን ፡ አቤቱ ፡ አቤቱ ፡ ባንተ ፡ ፊት ፡ ማን ፡ ይቆማል ።

፻፬ ፤ የብርሃን ፡ ሰንበት ፡ በሆነች ፡ ሥጋህና ፡ ደምህ ፡ በተሠራባት ፡ በዚህች ፡ ቀን ፡ ዛሬ ፡ ስማቸውን ፡ የምናውቃቸውን ፡ በዚህ ባገልጋዩ ፡ ቃል ፡ እንጠራለን ። ስማቸውንም የማናውቃቸውን ፡ አንተ ፡ በምሕረትህ ፡ አስባቸው ። ስማቸውንም ፡ ነፃ ፡ በምታደርግ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፍ ።

፻፮ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በእንተ ፡ ብፁዕ ፡ (ቅዳሴ ሐዋ ፡ ቍ ፡ ፯ ፡ ፱ ፡ ተመልከት ።)
፻፯ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ንፍቅ ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ።
(ቅዳሴ ፡ ሐዋ ፡ ቍ ፡ ፲ ፡ ፳፩ ፡)

፻፯ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፡ አቤቱ ፡ የጳጳሳቱን ፡ አለቆች ፡ ጳጳሳቱንና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳቱን ፡ ቀሳውስቱንና ፡ ዲያቆናቱን ፡ የክርስቲያንንም ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ማራቸው ፤ ይቅርም ፡ በላቸው ።

፻፰ ፤ ይ ፡ ካ ፡ በዚህ ፡ ቅዳሴህ ፡ ፊት ፡ ስብሐት ፡ አኰቴት ፡ ልዕልናም ፡ አሉ ። የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለጌትነትህ ፡ መጠን ፡ የለውም ፡ ለመንግሥትህም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፤ ለአገዛዝህም ፡ ወሰን ፡ የለውም ፡ ለግዛትህም ፡ ዳርቻ ፡ የለውም ።

፻፱ ፡ መለኮትህ ፡ የሚገኝበት ፡ አናኗርህም ፡ የሚወሰንበት ፡ አይታወቅም ፤ መለኮትህ ፡ የሚገኝበት ፡ አይመረመርም ፡ ባሕርይህም ፡ የሚደነገግበት ።

፻፲ ፤ ኢይበጽሖ ፡ ኅሊና ፡ ሰብእ ፡ ለቅ
ድምናከ ፡ ወኢይረክቦ ፡ ሥረተ ፡ መላእ
ክት ፡ ለደኃሪትከ ፡ ሥውር ፡ አንተ ፡ እምዓ
ይነ ፡ ኵሉ ፡ ወስሙዕ ፡ አንተ ፡ ውስተ ፡
እዝነ ፡ ኵሉ ።

፻፲፩ ፤ ርኁቅ ፡ አንተ ፡ ወምጡቅ ፡ እም
ዓይነ ፡ ኵሉ ፡ ወቅሩብ ፡ አንተ ፡ በኀቤሆሙ
ለእለ ፡ ይፈርሁከ ፡ ኵሉ ፡ ወምስሌሆሙ ፡
ተዐርፍ ፡ ወትገብር ፡ ሎሙ ፡ ፈቃዶሙ ።

፻፲፪ ፡ አ ፡ ዘኢትፈቅድ ፡ ዘኃጥእ ፡ ሞተ ፡
አላ ፡ ግብዓተ ።

፻፲፫ ፤ አ ፡ ዘታወፅአ ፡ ለሕፃን ፡ እምሐቌ ፡
ብእሲ ፡ ወትፌንዎ ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ፡ ብእ
ሲት ፡ ወትጠበልሎ ፡ በሰፋድል ፡ ረቂቅ ፡
ወእንዘ ፡ ማይ ፡ ውእቱ ፡ ታረግዖ ፡ በጥበብከ
ወትነፍሕ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈሰ ፡ ሕይወት ፡
ወበ፵ ፡ ዕለት ፡ ትሠይም ፡ ዲቤሁ ፡ በዘኮነ ፡
ከዊኖ ፡ እመሂ ፡ ለብዕል ፡ ወለነድይ ፡
እመሂ ፡ ለጻዲቅ ፡ ወለተኃጉሎ ።

፻፲፬ ፤ ወካዕበ ፡ ታወፅአ ፡ እምህየ ፡ ወት
ከሥት ፡ አዕይንቲሁ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡
ምድረ ፡ ዘህየ ፡ ምግባዒሁ ፡ ወትከሥት ፡
አብቃዊሁ ፡ ወታኬልሖ ።
ወታንሰሐስሖ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡
ከመ ፡ ያእምር ፡ ጥበ ፡ እሙ ።

፻፲፭ ፤ አ ፡ ዘታልሕቆ ፡ ወታወረዝዎ ፡
ወታበጽሖ ፡ እስከ ፡ ርስዓን ።

፻፲፮ ፤ አ ፡ ዘታደምፆ ፡ ለነፋስ ፡ ዘእንበለ ፡
ርእይ ፡ ወታሐውሮ ፡ ለጊሜ ፡ ዘእንበለ ፡ ድምፅ ።

፻፲፯ ፤ አ ፡ ዘቦቱ ፡ መዝገበ ፡ ስብሐት ፡
ዘኢይመልዮ ፡ ኵሉ ፡ ስብሐት ።

፻፲፰ ፤ መኑ ፡ ከማከ ፡ መንበሮ ፡ ዘከለለ ፡
በእሳት ፡ ወውስተ ፡ ልብሱ ፡ ዘገብረ ፡
ሥዕለ ፡ ማያት ፡ መኑ ፡ ከማከ ፡ ዘደለዎሙ ፡
ለአድባር ፡ በመዳልው ፡ ወለማየ ፡ ባሕርኒ ፡
ዘይሰፍሮ ፡ በሕፍኑ ።

፻፲፱ ፤ መኑ ፡ ከማከ ፡ ዘይጠፍር ፡ በማይ ፡
ጽርሖ ፡ ወአዕዋዲሁ ፡ በእሳት ፡ ዘተኬነወ ፡
ኢጠፈረ ፡ ማይ ፡ ዘላዕሉ ፡ ኢይወርድ ፡ ኀበ ፡
አዕዋደ ፡ እሳት ፡ በጥበብከ ፡ ወኢአዕዋደ ፡
እሳት ፡ ዘታሕቱ ፡ ኢየዐርግ ፡ ኀበ ፡ ጠፈረ ፡
ማይ ፡ ዘሀላዌከ ።

፻፲ ፡ ቅድምናህን ፡ የሰው ፡ አሳብ ፡ አይ
ደርስበትም ፤ ደኃራዊነትህንም ፡ የመላእ
ክት ፡ ፍጥነት ፡ አያገኘውም ። አንተ ፡ ከሁሉ
ዓይን ፡ የተሠወርህ ፡ ነህ ፡ በሁሉ ፡ ጆሮም ፡
የምትሰማ ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፻፩ ፤ አንተ ፡ ከሁሉ ፡ ዓይን ፡ ርኁቅ ፡
ምጡቅም ፡ ነህ ፡ አንተን ፡ በሚፈሩ ፡ ሁሉ ፡
ዘንድ ፡ አንተ ፡ የቀረብህ ፡ ነህ ፡ ከርሳቸ
ውም ፡ ጋራ ፡ ትኖራለህ ፤ ፈቃዳቸውንም ፡
ታደርግላቸዋለህ ።

፻፲፪ ፡ የኃጥእን ፡ መመለሱን ፡ እንጂ ፡
ሞቱን ፡ የማትወድ ፡ ሆይ ።

፻፲፫ ፤ ሕፃንን ፡ ከባቱ ፡ ወገብ ፡ አውጥ
ተህ ፡ ወደ ፡ ሴት ፡ ማኅፀን ፡ የምትልከው ፡
ሆይ ፡ በረቂቅ ፡ ሰፋድልም ፡ የምትጠቀል
ለው ፡ ውኃም ፡ ሲሆን ፡ በጥበብህ ፡ የምታረ
ጋው ። የሕይወት ፡ መንፈስንም ፡ እፍ ፡
ትልበታለህ ። በሆነ ፡ ሁኖ ፡ በዐርባ ፡ ቀን ፡
ትሾመዋለህ ፡ (ታድለዋለህ ።) ባለጸጋ ፡
ለመሆን ፡ ለመደህየትም ፡ ቢሆን ፡ ለመጽ
ደቅም ፡ ለመኰነንም ፡ ቢሆን ።

፻፲፬ ፤ ዳግመኛም ፡ ከዚያ ፡ ታወጣዋለህ ፤
ዓይኑንም ፡ ትገልጣለህ ፤ ከዚያ ፡ የሚገባበ
ትን ፡ ምድር ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ጕሮሮውን ፡
ከፍተህ ፡ ታስጮኸዋለህ ። እጁንና ፡ እግ
ሩን ፡ ታንቀሳቅሰዋለህ ፡ የእናቱን ፡ ጡት ፡
ያውቅ ፡ ዘንድ ።

፻፲፭ ፤ የምታሳድገውና ፡ የምታጐለምሰው
እስከ ፡ እርጅናም ፡ የምታደርሰው ፡ ሆይ ።

፻፲፮ ፤ ነፋስን ፡ ሳይታይ ፡ የምታሰማው ፡
ጉምንም ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ የምታስሄደው ፡ ሆይ ።

፻፲፯ ፤ ምስጋና ፡ ሁሉ ፡ የማይመላው ፡
የምስጋና ፡ መዝገብ ፡ ያለህ ፡ አቤቱ ።

፻፲፰ ፤ እንዳንተ ፡ ዙፋኑን ፡ በእሳት ፡
የጋረደ ፡ ማነው ፡ በልብሱስ ፡ የውኃ ፡
ሥዕል ፡ ያደረገ ፡ ማነው ። ተራራዎችንስ ፡
እንዳንተ ፡ በሚዛን ፡ የመዘናቸው ፡ የባሕ
ርንስ ፡ ውኃ ፡ በእፍኙ ፡ የሚሰፍረው ፡ ማነው ።

፻፲፱ ፤ እንዳንተ ፡ አዳራሹን ፡ በውኃ ፡
የሚታታ ፡ ዙሪያውንስ ፡ በእሳት ፡ የሠራ ፡
ማነው ። በላይ ፡ ያለው ፡ የውኃው ፡ ጠፈር ፡
በጥበብህ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ግርግዳ ፡ አይወር
ድም ። በታች ፡ ያለው ፡ የውኃው ፡ ግርግ
ዳም ፡ በአናንዋርህ ፡ በላይ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡
ውኃው ፡ ጠፈር ፡ አይወጣም ።

፻፳ ፤ መንክርኬ ፡ ወዕፁብ ፡ ወመድምም፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ምንተኑ ፡ እሔሊ ፡ ወእነክር ፡ ሀልዎተከኑ ፡ ምስለ ፡ አቡከ ፡ በአርምሞ ፡ ወበቅድስና ፡ ወሚመ ፡ ከመ ፡ ሕፃናት ፡ ውስተ ፡ ሕፅነ ፡ እምከ ።

፻፳፩ ፤ አየኑ ፡ እኄሊ ፡ ወእነክር ፡ ስብሐተኑ ፡ ዘይትፌኖ ፡ ለከ ፡ ከመ ፡ መዋግደ ፡ ባሕር ፡ እምኀበ ፡ ሱራፌል ፡ ወሚመ ፡ በውስተ ፡ ዮርዳኖስ ፡ እንዘ ፡ ትቀውም ፡ በትሕትና ።

፻፳፪ ፤ አ ፡ እግዚኦ ፡ እንዘ ፡ ሀሎከ ፡ በላዕሉ ፡ ትትበሐት ፡ በታሕቱ ፡ ወእንዘ ፡ ሀሎከ ፡ በታሕቱ ፡ ትሌለስ ፡ በላዕሉ ።

፻፳፫ ፤ ንህነሰ ፡ በአምጣነ ፡ ንክል ፡ ተናገርነ ፡ ወአብጻሕነ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ወእም ህየሰ ፡ ኢንክል ፡ ኀሊፈ ፡ እስመ ፡ ቦ ፡ ህየ ፡ ባሕረ ፡ እሳት ፡ ዘኢያበውሖ ፡ ለኀሊናነ ፡ ይዕዱ ። አንተ ፡ ለሊከ ፡ ተአምር ፡ ህላዌከ ፡ ወአንተ ፡ ለሊከ ፡ ትጤይቅ ፡ መለኮተከ ።

በዝየ ፡ ዕርገተ ፡ ዕጣን ።

፻፳፬ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ ተዘከረነ ፡ እግዚኦ ፡ በውስተ ፡ መንግሥትከ ።

፻፳፭ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ዘንተ ፡ ኅብስተ ፡ «እማሬ ፡» ዘዚአከ ፡ ሥጋ ፡ ናቀርብ ፡ ለከ ፡ ወዘንተ ፡ ጽዋዐ ፡ «እማሬ ፡» ዘዚአከ ፡ ደመ ፡ ናዐርግ ፡ ለከ ። በእንተ ፡ ኃጢአትነ ፡ ወአበሳነ ፡ ወበእንተ ፡ እበዶሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ አልቦ ፡ ዘኀባእከ ፡ እምነ ፡ አርዳኢከ ፡ ምሥጢረ ፡ ዕበያቲሁ ፡ ለመለኮትከ ።

፻፳፮ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ አንሥኡ ፡ እደዊክሙ ፡ ቀሳውስት ።

፻፳፯ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ነሣእከ ፡ ኅብስተ ፡ በቅድሜሆሙ ።

፻፳፰ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፡ ነአምን ።

፻፳፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ አእኰትከ ፡ ባረከ ። ቡራኬ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜ ወፈተትከ ።

፻፴ ፤ ወእምዝ ፡ ያንቅዖ ፡ ለኅብስት ፡ ለኀበ ፡ ፭ቱ ፡ ገጽ ፡ ንስቲተ ፡ እንዘ ፡ ኢይሌልዮ ። ወወሀብኮሙ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ንሥኡ ፡ ብልዑ ፡ ዝ ፡ ኅብስት ፡ «እማሬ ።» ሥጋየ ፡ ውእቱ ፡ ዘአልቦ ፡ ተሌልዮ ፡ እምኔሁ ።

፻፳ ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ የሚያስደንቅ ፡ ዕፁብ ፡ ነው ፤ ድንቅ ፡ ነው ፤ ማናቸውን ፡ አስቤ ፡ አደንቃለሁ ? በአርምሞና ፡ በቅድስና ፡ ካባትህ ፡ ጋራ ፡ መኖርህን ፡ ነውን ? ወይስ ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ በናትህ ፡ ክንድ ፡ መያዝህን ?

፻፳፩ ፤ ማናቸውን ፡ አስቤ ፡ አደንቃለሁ ? ከሱራፌል ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ማዕበል ፡ የሚቀርብልህን ፡ (የሚመጣልህን ፡) ምስጋና ፡ ነውን ? ወይስ ፡ በዮርዳኖስ ፡ በትሕትና ፡ መቆምህን ?

፻፳፪ ፤ አቤቱ ፡ በላይ ፡ ሳለህ ፡ በታች ፡ ብቸኛ ፡ ትሆናለህ ። በታች ፡ ሳለህም ፡ በላይ ፡ ሦስት ፡ ትሆናለህ ።

፻፳፫ ፤ እኛስ ፡ የተቻለንን ፡ ያህል ፡ ተናገርን ። እስከ ፡ ሰማይም ፡ አደረስን ። ከዚያ ፡ ማለፍ ፡ ግን ፡ አይቻለንም ። ይሻገር ፡ ዘንድ ኅሊናችንን ፡ የማያሰናብተው ፡ የእሳት ፡ ባሕር ፡ ከዚያ ፡ አለና ። አናንዋርህን ፡ አንተ፡ ራስህ ፡ ታውቃለህ ፤ መለኮትህንም ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ ትረዳለህ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዕጣኑን ፡ ያሳርግ ፡ (ቅዳሴ ፡ ሐዋ ፡ ቍ ፡ ፴፭ ። )

፻፳፬ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ በመንግሥትህ ፡ አስበን ።

፻፳፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ያንተ ፡ ሥጋ ፡ የሚሆን ፡ ይህን ፡ ኅብስት ፡ «እማሬ ፡» እናቀርብልሃለን ። ያንተ ፡ የሚሆን ፡ ይህንም ፡ ጽዋ ፡ «እማሬ ፡» እናሳርግልሃለን ። ስለ ፡ ኃጢአታችንና ፡ ስለ ፡ በደላችን ፡ ስለ ፡ ሕዝብህም ፡ ስንፍና ። ከደቀ ፡ መዛሙርትህ ፡ የሠወርከው ፡ የጌትነትህ ፡ ገናንነት ፡ ምሥጢር ፡ የለም ።

፻፳፮ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ቀሳውስት ፡ እጆቻችሁን ፡ አንሡ ።

፻፳፯ ፤ ይ ፡ ካ ፡ በፊታቸው ፡ ኅብስቱን ፡ አንሥተህ ፡ ያዝህ ።

፻፳፰ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ እናምናለን ፡ ይህ ፡ እርሱ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዕውነት ፡ እናምናለን ።

፻፳፱ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አመሰገንህ ፡ ባረክህ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ፡ ቆረስህ ።

፻፴ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኅብስቱን ፡ ሳይለየው ፡ ከአምስት ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ ያንቃው ።

ይህ ፡ ኅብስት ፡ «እማሬ ፡» ከርሱ ፡ መለየት ፡ የሌለበት ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡ ንሡ ፡ ብሉ ፡ ብለህ ፡ ሰጠሃቸው ።

፻፴፩ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ ነአምን ፡ ወንትአመን ፡ ንሴብሐከ ፡ አ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፡ ነአምን ።

፻፴፪ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ወከማሁ ፡ ጽዋዐኒ ፡ ቶሲ ሐከ ፡ ማየ ፡ ወወይነ ፡ አእኰትከ ፡ ባረከ ፡ ወቀደስከ ፡ ቡራኬ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜ ።

ወወሀብኮሙ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ንሥኡ ፡ ስትዩ ፡ ዝ ፡ ጽዋዕ ፡ «እግሬ ፡ » ደምየ ፡ ውእቱ ፡ ዘአልቦ ፡ ተፈልጠ ፡ እምኔሁ ።

ወይነክንኮ ፡ ለጽዋዕ ፡ በትእምርተ ፡ መስ ቀል ፡ በእዴሁ ፡ ዘየማን ።

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ።

፻፴፫ ፡ ይ ፡ ካ ፡ አምጣነ ፡ ትበልዕዎ ፡ ለዝ ንቱ ፡ ኅብስት ፡ ወትሰትይዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ጽዋዕ ፡ ዜንዉ ፡ ሞትየ ፡ ወትንሣኤየ ፡ ጠእ መኑ ፡ ዕርገትየ ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ፡ ወዳ ግመ ፡ ምጽአትየ ፡ በስብሐት ፡ እንዘ ፡ ትሴ ፈዉ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ንዜኑ ፡ ሞተከ ፡ እግዚኦ ፡ ወትን ሣኤከ ፡ ቅድሰተ ።

፻፴፬ ፤ ይ ፡ ካ ፡ በከመ ፡ ኢኀባእከ ፡ እምነ፡ አርዳኢከ ፤ ምሥጢረ ፡ ዕበያቲሁ ፡ ለመለ ኮትከ ፡ ወእሙንቱኒ ፡ አልቦ ፡ ዘኀብኡ ፡ እምኔነ ። ወሢሙነ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ኤጲስ ቆጶሳተ ፡ ቀሳውስተ ፡ ወዲያቆናተ ፡ ለሥር ዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንከ ።

፻፴፭ ፤ ወለዘሎሙ ፡ እለ ፡ ይትቃረንዋ ፡ ለሕግነ ፡ ሠሩ ፡ እምድር ፡ ዝክሮሙ ፡ ወኢ ትጽሐፍ ፡ ስሞሙ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕይወት ።

፻፴፮ ፤ ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ኢየኀብሩ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንከ ፡ ቅድስት ፡ ጉባኤ ፡ እንተ ፡ ሐዋርያት ፡ ስቅል ፡ ውስተ ፡ ክሣ ውዲሆሙ ፡ ጋጋ ፡ ዘእሳት ፤ ወቦኡ ፡ ይስ ሐቡ ፡ ውስተ ፡ ዐቢይ ፡ ሰይል ።

፻፴፯ ፡ ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይጸልኡ ፡ ስመከ ፡ ቅዱስ ፡ ምላኅ ፡ ሰይፈከ ፡ ወዕግ

፻፴፩ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ እናምናለን ፡ እንታመናለን ፡ ጌታችንና ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እናመሰግንሃለን ። ይህ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዕውነት ፡ እናምና ለን ።

፻፴፪ ፤ ይ ፡ ካ ፡ እንዲሁም ፡ ጽዋውን ፡ ውኃውንና ፡ ወይኑን ፡ ቀላቅለህ ፤ አመሰገ ንህ ፤ ባረክህ ፤ አከበርህም ። ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ፡ ይህ ፡ ጽዋ ፡ «እግሬ ፡ » ከርሱ ፡ መለየት ፡ የሌለበት ፡ ደሜ ፡ ነው ፡ ንሡ ፡ ጠጡ ፡ ብለህ ፡ ሰጠኻቸው ።

ጽዋውን ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ በዐራቱ ፡ ማዕ ዘን ፡ ይወዝውዘው ።

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ።

፻፴፫ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ይህን ፡ ኅብስት ፡ በምት በሉት ፡ ይህንም ፡ ጽዋ ፡ በምትጠጡት ፡ መጠን ፡ መሞቴንና ፡ መነሣቴን ፡ ንገሩ ፤ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ማረጌንም ፡ እመኑ ፡ ዳግ መኛ ፡ በክብር ፡ መምጣቴንም ፡ ተስፋ ፡ እያደረጋችሁ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ ሞትህን ፡ ቅድስት ፡ ትንሣኤህንም ፡ እንነግራለን ።

፻፴፬ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ከመለኮትህ ፡ ገናንነት ፡ ምሥጢር ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርትህ ፡ እንዳል ሠወርህ ፡ እነሱም ፡ ከእኛ ፡ የሠወሩት ፡ የለም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ቀሳውስት ዲያቆናት ፡ አድርገው ፡ ሾሙን ።

፻፴፭ ፤ ሕጋችንን ፡ የሚቃወሙአትንም ፡ ሁሉ ። ስም ፡ አጠራራቸውን ፡ ከምድር ፡ ነቅለህ ፡ አጥፋ ። ስማቸውንም ፡ በሕይወት ፡ መጻፍ  አትጻፍ ።

፻፴፮ ፤ ሐዋርያት ፡ አንድ ፡ ካደረጓት ፡ ከቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንህ ፡ ጋራ ፡ የማ ይተባበሩትንም ፡ ሁሉ ፡ በአንገታቸው ፡ የእሳት ፡ ዛንጅር ፡ ስቀልባቸው ። በርሱም ፡ ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ጠቅሶ ፡ ይሳቡ ።

፻፴፯ ፤ ቅዱስ ፡ ስምህን ፡ የሚጠሉትንም፡ ሁሉ ፡ ሰይፍህን ፡ መዘህ ፡ ክበባቸው ። የሚ

ቶሙ ፡ ወእንተ ፡ ይከይድዋ ፡ ምድር ፡ ለት
ሠረም ፡ ወተኀጦሙ ፤ ወይረዱ ፡ ውስተ ፡
ሲኦል ፡ ሕያዋኒሆሙ ።

፻፴፰ ፤ ንህነሰ ፡ እለ ፡ ትሰይድነ ፡ በእንተ፡
ስምከ ፡ ወኮነ ፡ ሕብልያ ፡ እምኀቤሆሙ ፡
ለዕልዋን ፡ ረዐየነ ፡ በግህልከ ፡ ከመ ፡ ነሐ
ድፍ ፡ ልቦሙ ፡ ለመሃይምናኒከ ።

፻፴፱ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ እግዚኦ ፡ መሐ
ረነ ፡ እግዚኦ ፡ መሐከነ ፡ እግዚኦ ፡ ተሣሃ
ለነ ።

፻፵ ፡ ይ ፡ ካ ፡ እስመ ፡ በዝኑ ፡ መከል
ኣን ፡ መሠጥ ፡ እለ ፡ ኢይምሕክዋ ፡ ለመር
ዔትከ ።

፻፵፩ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በኵሉ ፡ ልብ ፡ ናስተብ
ቍዖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ኅብ
ረተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሠናየ ፡ ከመ ፡ ይጸ
ግወነ ።

፻፵፪ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ በከመ ፡ ሀሎ ፡ ህልወ ፡
ወይሄሉ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ለዓለመ ፡
ዓለም ።

፻፵፫ ፤ በዝየ ፡ ይኀትም ፡ ሥጋ ፡ በደም ፡
ጠሚዖ ፡ በአጽባዕቱ ።

ይ ፡ ካ ፡ ደሚረከ ፡ ተሀቦሙ ፡ ለኵሎሙ ፡
እንዘ ፡ ትቄድሶ ፡ ለውእቱ ፡ በውእቱ ።

ቡራኬ ፡ አሐደ ፡ ላዕለ ፡ ኅብስት ፡ ወአሐደ ፡
ላዕለ ፡ ጽዋዕ ፡ ዳግመ ፡ ላዕለ ፡ ክልኤሆሙ ፡ አሐደ
ጊዜ ።

፻፵፬ ፤ ኦ ፡ ወልድ ፡ ከላሕ ፡ ከመ ፡
ዘሐመ ፡ ወበል ፡ ኤልማስ ፡ ላማ ፡ ሰበቅ
ታኒ ፡ ወእንዘ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ፡
በል ፡ አባ ፡ ወአቡየ ፡ መሐር ፡ ወተሣሃል ፡
እለ ፡ በልዑ ፡ ሥጋየ ፡ ወሰትዩ ፡ ደምየ ።

፻፵፭ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ሀበነ ፡ ንኅበር ፡ በዘዚ
አከ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወፈውሰነ ፡ በዝ
ንቱ ፡ ጵርስፎራ ፡ ከመ ፡ ብከ ፡ ንሕየው ፡
ዘለኵሉ ፡ ዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።
ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

፻፵፮ ይ ፡ ካ ፡ ቡሩክ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ ወቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡
እግዚአብሔር ፡ ወይትባረክ ፡ ስመ ፡ ስብ
ሓቲሁ ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ፡ ቡሩክ ፡ ለይ
ኩን ።
ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

ረግጧትም፡ ምድር ፡ ረግረግ ፡ ሁና ፡ ታስጥ
ማቸው ፡ በሕያውነታቸው ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡
ይውረዱ ።

፻፴፰ ፤ ስለ ፡ ስምህ ፡ የተሰደድን ፡ በዐ
ላውያን ፡ ዘንድ ፡ ብዝበዛ ፡ የሆነ ፡ እኛን ፡
ግን ፡ በይቅርታህ ፡ ጠብቀን ። የምዕመናን
ህን ፡ ልቡና ፡ እናጸና ፡ ዘንድ ።

፻፴፱ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ አቤቱ ፡ ማረን ፡
አቤቱ ፡ ራራልን ፡ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

፻፵ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ለመንጋህ ፡ የማይራሩለት ፡
የሚከለክሉ ፡ የሚነጥቁ ፡ ከልካዮች ፡ በዝተ
ዋልና ።

፻፵፩ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በፍጹም ፡ ልብ ፡ አምላ
ካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንማልደው ፡
ያማረ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አንድነት ፡
ይሰጠን ፡ ዘንድ ።

፻፵፪ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ ብፊት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡
ለዘላለሙ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይኖራል ።

፻፵፫ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በጣቱ ፡ ጠምቆ ፡
በደሙ ፡ ሥጋውን ፡ ይቀባ ።

ይ ፡ ካ ፡ እርሱን ፡ በርሱ ፡ አክብረህ ፡ ለሁ
ላቸው ፡ አንድ ፡ አድርገህ ፡ ትሰጣቸው ፡
ዘንድ ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኅብስቱን ፡ አንድ ፡
ጊዜ ፡ ጽዋውን ፡ ይባርክ ። ደግመኛ ፡ ሁለ
ቱንም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ።

፻፵፬ ፤ ወልድ ፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፡
ሰው ፡ አሰምተህ ፡ ተናገር ፡ ኤልማስ ፡ ላማ
ሰበቅታኒ ፡ በል ። በአፋቸውም ፡ ውስጥ ፡
ሳለ ፡ አባ ፡ አባቴም ፡ ሆይ ፡ ሥጋዬን ፡ የበሉ
ትን ፡ ደሜን ፡ የጠጡትን ፡ ማራቸው ፡ ይቅር
በላቸው ፡ በል ።

፻፵፭ ፡ ይ ፡ ካ ፡ የአንተ ፡ በሚሆን ፡ በመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡
መሆንን ፡ ስጠን ። በዚህም ፡ ጵርስፎራ ፡
(በሥጋው ፡ በደሙ ፡) አድነን ፡ በአንተ ፡
ለዘላለሙ ፡ ሕያዋን ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ።
ይ ፡ ሕ ፡ እንደርሱ ።

፻፵፮ ፡ ይ ፡ ካ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስሙ ፡
ምስጉን ፡ ነው ። በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡
የሚመጣውም ፡ ምስጉን ፡ ነው ። የጌትነቱ ፡
ስም ፡ ይመስገን ። ይሁን ፡ ይሁን ፡ የተመሰ
ገነ ፡ ይሁን ።
ይ ፡ ሕ ፡ እንደርሱ ።

፻፵፯ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ፈኑ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌነ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

፻፵፰ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።

ይ ፡ ሕ ፡ እግዚኦ ፡ ተሣሃለነ ።

ይ ፡ ካ ፡ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፻፵፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ጸሎተ ፡ ፈትቶ ።

ወካዕበ ፡ ናስተበቍዖ ፡ ለአምላክ ፡ ምሕረት ። ወሎቱ ፡ ንትከሀን ፡ ዘውእቱ ፡ ካህን ፡ ወሎቱ ፡ ንሡዕ ፡ ዘውእቱ ፡ መሥዋዕት ፡ ወሎቱ ፡ ናቀርብ ፡ ዘውእቱ ፡ መቅርብ ።

፻፶ ፡ ይምጻእ ፡ ውእቱ ፡ በግዕ ፡ እመልዕልተ ፡ መልዕልት ፡ ንርአዮ ፡ በአዕይንቲ ፡ ወንጥብሖ ፡ በእእዳው ፡ ከመ ፡ ንትፈሣሕ ፡ ቦቱ ።

፻፶፩ ፡ ይደመር ፡ ሥጋሁ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ኅብስት ፡ ወደሙኒ ፡ ይትከዐው ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ጽዋዕ ።

፻፶፪ ፡ ወኢይምሰሎ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔነ ፡ ሶበ ፡ ይበልዕ ፡ ዘንተ ፡ ኅብስተ ፡ ከመ ፡ ዘይበልዕ ፡ ሥጋ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘእንበለ ፡ ደም ፡ ወመንፈስ ፡ ወሶበ ፡ ይሰቲ ፡ ዘንተ ፡ ጽዋዐ ፡ ኢይምሰሎ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔነ ፡ ከመ ፡ ዘይሰቲ ፡ ደመ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘእንበለ ፡ ሥጋ ፡ ወመንፈስ ፡ አላ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋ ፡ ወደም ፡ ወመንፈስ ።

፻፶፫ ፡ በከመ ፡ ኮነ ፡ መለኮቱ ፡ ዘምስለ ፡ ትስብእቱ ፡ ፩ደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ።

፻፶፬ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ጸልዩ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ።

፻፶፭ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ንስእለከ ፡ አ ፡ አብ ፡ ወናስተበቍዕ ፡ እምነ ፡ ኂሩትከ ፡ ከመ ፡ ትፈኑ ፡ ወልደከ ፡ ወፍቁረከ ፡ ዘአልቦ ፡ አሠር ፡ ለህላዌሁ ፡ እንዘ ፡ እሳተ ፡ መለኮት ፡ ውእቱ

፻፵፯ ፡ ይ ፡ ካ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ጸጋ ፡ ላክልን ።

ይ ፡ ሕ ፡ እንደርሱ ።

፻፵፰ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ለጸሎት ፡ ተነሡ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይ ፡ ካ ፡ ሰላም ፡ ለሁላችሁ ፡ ይሁን ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከመንፈስህ ፡ ጋራ ።

፻፵፱ ፡ ይ ፡ ካ ፡ የመፈተት ፡ ጸሎት ።

ዳግመኛም ፡ የምሕረትን ፡ አምላክ ፡ እንማልደዋለን ። አገልጋይ ፡ ለሚሆን ፡ ለርሱ ፡ እናገለግላለን ። መሥዋዕት ፡ ለሚሆን ፡ ለርሱ ፡ እንሠዋለን ፡ ለሚቀርብ ፡ ለርሱ ፡ እናቀርባለን ።

፻፶ ፡ በግዕ ፡ እርሱ ፡ ከሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ይምጣ ። በዓይናችን ፡ ዐይተን ፡ በእጃችን ፡ ሠውተን ፡ ደስ ፡ እንሰኝበት ፡ ዘንድ ።

፻፶፩ ፡ ሥጋው ፡ ከዚህ ፡ ኅብስት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ይሁን ፡ ደሙም ፡ ከዚህ ፡ ጽዋ ፡ ይቀዳ ።

፻፶፪ ፡ ይህን ፡ ኅብስት ፡ በሚበላበት ፡ ጊዜ ከእኛ ፡ ወገን ፡ ላንዱ ፡ ያለ ፡ ደምና ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ሥጋን ፡ ብቻ ፡ የሚበላ ፡ አይምሰለው ። ይህነንም ፡ ጽዋ ፡ በሚጠጣበት ፡ ጊዜ ፡ ከእኛ ፡ ላንዱ ፡ ያለ ፡ ሥጋና ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ደምን ፡ ብቻ ፡ የሚጠጣ ፡ አይምሰለው ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ መንፈስም ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ።

፻፶፫ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ መለኮቱ ፡ ከትስብእቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንደ ሆነ ።

፻፶፬ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ጸልዩ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ። ( ቅ ፡ ሐዋ ቍ ፡ ፳ ። )

፻፶፭ ፡ ይ ፡ ካ ፡ አብ ፡ ሆይ ፡ እንለምንሃለን ፡ ከቸርነትህም ፡ እንማልዳለን ፡ እሳተ ፡ መለኮት ፡ ሲሆን ፡ ለባሕርዩ ፡ ፍጻሜ ፡ የለ ለውን ፡ ልጅህን ፡ ወዳጅህን ፡ ትሰድልን ዘንድ ።

፻፶፯ ፤ እስኩኬ ፡ ንርአዮ ፡ ለዘይመስል ፡ እሳተ ፡ ለሕርደት ፡ መንፈሳዊ ፡ ወለጥብሕ ፡ ነባቢ ፡ ይደመር ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ አኰቴት ፡ ውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

፻፶፰ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ ሠራዊተ ፡ መላእክቲሁ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ይቀውሙ ፡ ቅድሜሁ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ።

ወይኬልልዎ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ።

ወንብጻሕ ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ በአሚነ ፡ ዚአሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንጉሥ።

፻፶፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፤ አርኅዉ ፡ ኆኃተ ፡ መኳንንት ።

፻፷ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ እለ ፡ ትቀውሙ ፡ አትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ።

፻፷፩ ፡ ይ ፡ ካ ፡ አ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ ሰንበተ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ ስብሕት ፡ ከመ ፡ አብ ፡ ስፍንት ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ ህሉት ፡ ከመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ ሰንበተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ ሰአሊ ፡ ለነ ፡ አስተምሕሪ ፡ በእንቲአነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

፻፷፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ስግዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሃት ።

ይ ፡ ሕ ፡ ቅድሜከ ፡ እግዚኦ ፡ ንሰግድ ፡ ወንሴብሐከ ።

፻፷፫ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ጸሎተ ፡ ንስሐ ።

፻፷፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ነጽር ።

ይ ፡ ካ ፡ ቅድሳት ፡ ለቅዱሳን ።

ይ ፡ ሕ ፡ ፩ዱ፡አብ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ ወልድ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ፡ውእቱ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፻፷፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፻፷፮ ፤ ወእምዝ ፡ ያንሥእ ፡ ካህን ፡ ኅብስተ ፡ ፍጹመ ፡ በእዴሁ ፡ ወይበል ።

እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜ ፡ በልዑል ፡ ዜማ ። ፲ተወ፫ተ ፡ ጊዜ ፡ በንዑስ ፡ ዜማ ።

፻፶፯ ፤ እሳት ፡ የሚመስል ፡ መንፈሳዊና ፡ ነባቢ ፡ መሥዋዕትን ፡ እስኪ ፡ እንየው ፡ እርሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡ በመሥዋዕቱ ፡ ላይ ፡ ይደር ፡ ለዘላለሙ ።

፻፶፰ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ የመላእክት ፡ ሠራዊት ፡ በመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ፊት ፡ ይቆማሉ ።

መድኃኔ ፡ ዓለምን ፡ ያመሰግኑታል ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ሥጋውና ፡ ደሙ ።

ወደ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ፊት ፡ እንቅረብ ።

እርሱን ፡ በማመን ፡ ለክርስቶስ እንገዛ ።

፻፶፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፡ መኳንንት ፡ ደጆችን ፡ ክፈቱ ።

፻፷ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ የቆማችሁ ሰዎች ፡ ራሳችሁን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ።

፻፷፩ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ክብርት ፡ የምትሆን ፡ ይህች የክርስቲያን ፡ ሰንበት ፡ ምን ፡ ትደንቅ ። እንደአብ ፡ የሠለጠነች ፡ እንደ ፡ ወልድ ፡ የምትገዛ ፡ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የምትኖር ፡ ናት ፡ ይህች ፡ ቅድስት ፡ የክርስቲያን ፡ ሰንበት ፡ ምን ፡ ትደንቅ ፤ ከአምላካችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለምኝልን፡ስለኛም አማልጂ ፡ ለዘላለሙ ።

፻፷፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ በፍርሃት ፡ ሁናችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስገዱ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ በፊትህ ፤ እንሰግዳለን ፡ እናመሰግንሃለንም ።

፻፷፫ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ጸሎተ ፡ ንስሐ ፡ (ቅዳ ፡ ሐዋ ፤ ቍ ፡ ፸፱—፹፰ ።)

፻፷፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ተመልከት ።

ይ ፡ ካ ፡ ቅድሳት ፡ ለቅዱሳን ።

ይ ፡ ሕ ፡ ቅዱስ ፡ አብ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ቅዱስ ፡ ወልድም ፡ አንድ ፡ ነው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አንድ ፡ ነው ።

፻፷፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሁላችሁ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከመንፈስህ ፡ ጋራ ።

፻፷፮ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ቄሱ ፡ መላውን ፡ ኅብስት ፡ አንሥቶ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ እንዲህ ይበል ።

አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ። ፫ ፡ ጊዜ ፡ በከፍተኛ ፡ ዜማ ። ፲፫ ፡ ጊዜም ፡ በንዑስ ፡ ዜማ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

ወእምዝ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜ ። ይ ፡ ሕ ፡ ፪ኤተ ፡ ጊዜ ።

፻፳፯ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ንስሓ ፡ ሀለውክሙ ፡ አተሕቱ ፡ ርእሰክሙ ።

፻፳፰ ፡ ወእምዝ ፡ ተመይጦ ፡ መንገለ ፡ ሕዝብ ።

ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ነጽር ፡ ዲበ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ንስሓ ፡ ሀለዉ ።

፻፳፱ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተመጠዉ ።

ይ ፡ ካ ፡ ኃዳፌ ፡ ነፍስ ። በከመ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ በመዝሙር ፡ እግዚኦ ፡ መኑ ፡ የኀድር ፡ ውስተ ፡ ጽላሎትከ ፤ ወመኑ ፡ ያጸልል ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ መቅደስከ ።

፻፴ ፡ ተሠጥወ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤ ። ዘየሐውር ፡ በንጹሕ ፡ ወይገብር ፡ ጽድቀ ። ወዘይነብብ ፡ ጽድቀ ፡ በልቡ ። ወዘኢኀሕለወ ፡ በልሳኑ ። ወዘኢገብረ ፡ እኩየ ፡ ዲበ ፡ ቢጹ ። ወዘኢያጽአለ ፡ አዝማዲሁ ። ወዘምኑን ፡ በቅድሜሁ ፡ እኩይ ። ዘያከብሮሙ ፡ ለፈራህያነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይምሕል ፡ ለቢጹ ፡ ወኢይሔሱ ። ወዘኢለቅሐ ፡ ወርቆ ፡ በርዴ ። ወዘኢነሥአ ፡ ሕልያነ ፡ በላዕለ ፡ ንጹሕ ። ዘይገብር ፡ ከመዝ ፡ ኢይትሀወክ ፡ ለዓለም ።

፻፴፩ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ መኑ ፡ የዐርግ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወመኑ ፡ ይቀውሙ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ መቅደሱ ።

፻፴፪ ፡ ተሠጥወ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤ ። ዘንጹሕ ፡ ልቡ ፡ ወንጹሕ ፡ እደዊሁ ፡ ወዘኢነሥአ ፡ ከንቶ ፡ በላዕለ ፡ ነፍሱ ። ወዘኢመሐለ ፡ በጕሕሉት ፡ ለቢጹ ። ውእቱ ፡ ይነሥእ ፡ በረከተ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይበውእ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ እንተ ፡ ኪያሃ ፡ ወገባሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ይ ፡ ዲ ፡ ጸልዩ ።

፻፴፫ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ንዑ ፡ ናዕብያ ፡ ንዑ ፡ ንወድሳ ፡ ንዑ ፡ ናክብራ ፡ ንዑ ፡ ናብዕላ ፡ ለበዓለ ፡ በዓላት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሰንበተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ።

ይ ፡ ሕ ፡ እንደርሱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ። ይ ፡ ሕ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ።

፻፳፯ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በንስሐ ፡ ውስጥ ፡ ያላችሁ ፡ ራሳችሁን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ።

፻፳፰ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ተመልሶ ።

ይ ፡ ካ ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፡ በንስሓ ፡ ወዳሉት ፡ ወገኖች ፡ ተመልከት ፡ (ቅዳሴ ፡ ሐዋ ፡ ቍ ፡ ፺፫—፺፯ ።)

፻፳፱ ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ።

ይ ፡ ካ ፡ ኃዳፌ ፡ ነፍስ ። ዳዊት ፡ በመዝሙር ፡ እንደተናገረ ፡ አቤቱ ፡ በጥላህ ፡ ማን ፡ ያድራል ። በመቅደስህስ ፡ ተራራነት ፡ ማን ፡ ያርፋል ።

፻፴ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ። በንጽሕና ፡ የሚኖር ፡ ጽድቅንም ፡ የሚሠራ ፡ ነው ። በልቡናው ፡ እውነትን ፡ የሚናገር ፤ በአንደበቱ ፡ ያልሸነገለ ፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ያላደረገ ፤ ዘመዶቹን ፡ ያላሰደበ ። ክፉ ፡ ነገር ፡ በፊቱ ፡ የተናቀ ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩትን ፡ ሰዎች የሚያከብራቸው ፡ ባልንጀራውን ፡ ምሎ ፡ የማይከዳ ፤ ወርቁን ፡ በአራጣ ፡ ያላበደረ ፤ በንጹሑ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ማማለጃን ፡ ያልተቀበለ ፤ እንዲህ ፡ የሚያደርግ ፡ ለዘላለሙ ፡ አይታወክም ።

፻፴፩ ፡ ዳግመኛም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ ማን ፡ ይወጣል ፡ በመቅደሱስ ፡ ቦታ ማን ፡ ይቆማል ፡ አለ ።

፻፴፪ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡ ልቡ ፡ ንጹሕ ፡ እጁም ፡ ንጹሕ የሆነ ፡ ነው ፤ በሰውነቱ ፡ ላይ ፡ ከንቱን ፡ ነገር ፡ ያልተቀበለ ፡ ለባልንጀራው ፡ በሽንገላ ፡ ያልማለ ፤ እርሱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በረከትን ፡ ይቀበላል ። ሠሪዋ ፡ ተጠባቢዋ ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ሚሆን ፡ አገር ፡ ይገባል ።

ይ ፡ ዲ ፡ ጸልዩ ።

፻፴፫ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ኑ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እናድርጋት ፡ ኑ ፡ እናመስግናት ፡ ኑ ፡ እናክብራት ፡ ኑ ፡ በዓል ፡ እናድርጋት ፤ የበዓላትን ፡ መጀመሪያ ፡ ይህችውም ፡ ክብርት ፡ የምትሆን ፡ የክርስቲያን ፡ ሰንበት ፡ ናት ።

፻፸፫ ፤ በከመ ፡ ተፈሣሕነ ፡ ትማልም ፡ በበዐታ ፡ ከማሁ ፡ ናስተፋንዋ ፡ በፍሥሓ ፡ በፀአታ ፡ እንዘ ፡ ንትማህ ፡ ባቲ ፡ በአዕርፎ ፡ ሥጋነ ።

፻፸፬ ፤ ወዕረፍትነሰ ፡ አኮ ፡ በሰኪብ ፡ ከመ ፡ ዘሐመ ፡ በደዌ ፡ አላ ፡ በትጋህ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ከመ ፡ ንኩን ፡ ፍቁራኒሃ ፡ ለዛቲ ፡ ዕለት ።

፻፸፭ ፤ ወካዕበ ፡ ንበል ፡ ሰአሊ ፡ ለነ ፡ አስተምሕሪ ፡ በእንቲአነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ለእለ ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ እንስሳ ፡ ወአከይነ ፡ እምኔሆሙ ።

፻፸፮ ፤ አ ፡ ቅድስት ፡ ንዒ ፡ ኀቤነ ፡ ለለ ፡ ሰሙኑ ፡ ከመ ፡ ንትፌሣሕ ፡ ብኪ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።

፻፸፯ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አንብሮ ፡ እድ ። ክህናትየ ፡ ይቤሎሙ ፡ ፈድፋደ ፡ እምዘቱ ፡ አፍቀሮሙ ፡ ዘኢተገብረ ፡ ለመላእክት ፡ ተገብረ ፡ ለካህናት ።

፻፸፰ ፤ ዘተመጠነ ፡ በእደዊሆሙ ፡ ለካህናት ፡ ዘንተ ፡ ሥጋ ፡ ወልድከ ፡ ቅዱስ ፡ ወደመ ፡ መሢሕከ ፡ ክቡር ፡ አ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ረሲ ፡ ይኩነነ ፡ ለሕይወት ፡ ወለመድኃኒት ፡ ወለሥርየተ ፡ ኃጢአት ፡ ወለሕይት ፡ ዘኢየኀልቅ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፻፸፫ ፤ ትናንት ፡ በመግባትዋ ፡ ደስ ፡ እንዳለን ፡ እንዲሁ ፡ በመውጣትዋ ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ እንሸኛት ፤ በርስዋ ፡ ሥጋችንን ፡ በማሳረፍ ፡ እየተጋን ።

፻፸፬ ፤ ዕረፍታችን ፡ ግን ፡ በደዌ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፡ ሰው ፡ በመተኛት ፡ አይደለም ፤ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ በመትጋት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የዚህች ፡ ዕለት ፡ ወዳጆችዋ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ

፻፸፭ ፤ ዳግመኛም ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ ለሆነ ፡ ከእንስሳትም ፡ ለከፋን ፡ ለእኛ ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለምኝልን ፡ ስለኛ ፡ አማልጂ ፡ እንበል ።

፻፸፮ ፤ ቅድስት ፡ ሆይ ፡ በየሳምንቱ ፡ ወደኛ ፡ ነዪ ፡ በአንቺ ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡ ለዘለዓለሙ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።

፻፸፯ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አንብሮ ፡ እድ ። አገልጋዮቼ ፡ አላቸው ፤ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ወደዳቸው ለመላእክት ፡ ያልተደረገ ፡ ለካህናት ፡ ተደረገ ።

፻፸፰ ፤ በካህናት ፡ እጅ ፡ የተቀበልነውን ፡ ይህን ፡ ቅዱስ ፡ የሚሆን ፡ የልጅህን ፡ ሥጋ ፤ የመሢሕህንም ፡ ክቡር ፡ ደም ፤ በሰማይ ፡ የምትኖር ፡ አባታችን ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፡ ለሕይወትና ፡ ለመድኃኒት ለኃጢአት ፡ ማስተሥረያና ፡ ለማያልቅ ፡ ኑሮ ፡ እንዲሆነን  አድርግ ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።